ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 223 ሚያዝያ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






## ‹‹ኢትዮጵያን ከኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት በማላቀቅ ነፃነቷን ምሉዕ ለማድረግ መትጋት ያስፈልጋል››

-ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያን ከኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት በማላቀቅ ነፃነቷን ምሉዕ ለማድረግ መትጋት ያስፈልጋል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

የለውጡን መንግሥት የሚደግፍ ሕዝባዊ መድረክ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት ትላንት በወልቂጤ ከተማ ተካሂዷል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወቅቱ ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት፡-ኢትዮጵያ ለነፃነቷ የተጋደለችና ያልተገዛች ሀገር ብትሆንም ከኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት በመላቀቅ ነፃነቷን ምሉዕ ለማድረግ መትጋት ያስፈልጋል።

ጉራጌ ጎጎት በተባለው ቃል ኪዳኑ ስለ አንድነትና አብሮነት አበክሮ ያስተማረና በተግባር የኖረ ማኅበረሰብ

‹‹ኢትዮጵያን...ወደ ገጽ 5 ዞሯል







## በአማራ ክልል ከሦስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ ነው

### - በመጪው የመኸር ወቅት 169 ሚሊዮን ኩንታል ለማግኘት ታቅዷል

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ለመጪው የመኸር ወቅት ከሦስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። ክልሉ በመኸር ወቅት ከአምስት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በማረስ 169 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ዕቅድ መያዙንም ተጠቁሟል።

በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የሰብል ልማትና ጥበቃ ዳይሬክተር ማንደፍሮ አስናቀ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ቢሮው ለመጪው የመኸር ወቅት በግብዓትነት እንዲውል ግዢ ከፈጸመው ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ውስጥ ከሦስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ ነው።

በአማራ ክልል...ወደ ገጽ 5 ዞሯል




## የኤች አይ ቪ/ኤድስ የግንዛቤ ፈጠራ አሁንም ትኩረት ይሻል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**




አዲስ አበባ፡- ስለኤች አይቪ/ኤድስ ስርጭት የሚሰጠው የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ከጊዜ ወደጊዜ እየተቀዛቀዘ በመሆኑ ችግሮች ከመባባሳቸው በፊት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ ተገለጸ።

በጤና ሚኒስትር የኤች አይቪ ኤድስ መከላከልና

የኤች ኤይ ቪ/ኤድስ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## ለውጪ ገበያ ከቀረቡ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች 23 ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኘ

### -የገበያ መቀዛቀዝ ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ገቢ ቅናሽ አሳይቷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ለውጭ ገበያ ከቀረቡ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች 23 ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከል አስታወቀ። የምርት መዳረሻ ሀገራት ገበያ በመቀዛቀዙ ከቆዳ ዘርፉ ለማግኘት የታቀደውን ገቢ ማሳካት አለመቻሉም ተመላክቷል።

የማዕከሉ ተወካይ ሥራ አስኪያጅ አቶ መሐመድ ሁሴን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በበጀት

ለውጪ ገበያ ከቀረቡ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ዜና



# በዞኑ በመጪው ክረምት 700 ሺህ የቴምር ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- በመጪው የክረምት ወቅት 700 ሺህ የቴምር ችግኞችን ለመትከል መታቀዱን የምሥራቅ ሸዋ ዞን ግብርና ጽሕፈት ቤት አስታወቀ ፡፡

በኦሮሚያ ክልል የምሥራቅ ሸዋ ዞን ግብርና ጽሕፈት ቤት ቢሮ ኃላፊ አቶ መስፍን ተሾመ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዞኑ ባለፈው ዓመት ቴምርን ለማልማት ሙከራ አድርጓል። በዚህም 30 ሺህ የቴምር ችግኞች ተተክለው አሁን በጥሩ ሁኔታ ላይ ናቸው ፡፡

የዓምናውን ተሞክሮ በመውሰድ በዘንድሮ ክረምት 700 ሺህ የቴምር ችግኞችን ለመትከል ዝግጅት ተጠናቋል ያሉት አቶ መስፍን፤ ችግኞቹ በ64 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ እንደሚተከሉ ገልጸዋል ፡፡

ችግኞቹ ለመትከል ዝግጅት የተደረገው በፈንታሌ እና ቦሰት ወረዳዎች መሆኑን ገልጸው፤ እነዚህ አካባቢዎች ለተክሉ ምቹ የአየር ንብረት ያላቸው መሆኑን ተናግረዋል።

በሀገራችን ቴምርን ለማምረት የማያስችል የአየርም ሆነ የውሃ ችግር የለም ያሉት አቶ መስፍን፤ ማኅበረሰቡ ላይ ያለው ግንዛቤ አናሳ ነው ብለዋል ፡፡

ቴምር በተለምዶ እንደሚባለው 15 እና 20 ዓመት የሚፈጅ ተክል ሳይሆን በአምስት ዓመት ውስጥ ምርት መስጠት የሚችል መሆኑንም አብራርተዋል ፡፡

ለመትከል የተዘጋጁት ችግኞች የተሻሻሉ ዝርያዎች በመሆናቸው ጥሩ ውጤት ይጠበቃል ያሉት አቶ መስፍን፤ ምርቱን ለማሳደግም በግለሰብ ደረጃ ሁሉም ማኅበረሰብ በየጓሮው ቢተክለው የበለጠ ውጤታማ ይሆናል ብለዋል ፡፡

እንደ አቶ መስፍን ገለጻ፤ ግብርና አራት ትኩረት አቅጣጫዎችን ይዞ የሚሠራ ዘርፍ ነው። ከእነዚህ መካከል ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን መጨመር እና ወደ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን መተካት ይገኙበታል። በዚህም በቀጣይ የቴምር ምርትን በስፋት በማምረት ሀገራችን ቴምርን ወደ ሀገር በማስገባት የምታወጣውን ከፍተኛ ውጭ ምንዛሪ ማስቀረት ይቻላል ብለዋል።

# የቡልቡላ-አላጌ-ሚቶ የኮንክሪት አስፋልት መንገድ ግንባታ 62 በመቶ ደረሰ

ታደሠ ብናልፈው



አላጌ፡- በ878 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ እየተገነባ ያለው የቡልቡላ-አላጌ-ባራ-ሚቶ የኮንክሪት አስፋልት መንገድ ግንባታ አፈጻጸም 62 በመቶ መድረሱን የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አስታወቀ።

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የቡታጅራ አካባቢ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ገዛኸኝ ዋቅቶሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልልን ከኦሮሚያ የሚያገናኝ በ878 ሚሊዮን 514 ሺህ 732 ብር በላይ ወጪ እየተሠራ ያለው የቡልቡላ-አላጌ -ባራ-ሚቶ የኮንክሪት አስፋልት የግንባታ ሂደት ከ62 በመቶ በላይ ደርሷል። መንገዱ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልልን ከኦሮሚያ ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡

ፕሮጀክቱ መነሻውን ቡልቡላ በማድረግ በስፍራው የሚገኙ ቡልቡላ-ጂዶ- አላጌ ግብርና ኮሌጅ-ሚቶ ከተማን የሚያልፍ ሲሆን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣይ በጀት ዓመት ሙሉ ለሙሉ የመንገድ ግንባታው እንደሚጠናቀቅ አመልክተዋል።

የመንገዱ ፕሮጀክት ተገንብቶ ሲጠናቀቅና አገልግሎት መስጠት ሲጀምር ከዚህ በፊት ከቡልቡላ- አላጌ ከተማ ለመጓዝ የሚፈጀውን የሁለት ሰዓት የጉዞ ጊዜ ወደ ግማሽ ሰዓት ዝቅ እንደሚያደርገው ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ የአካባቢው አርሶ አደሮች የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ትልቅ አስተዋፅዖ ያበረክታል ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ በአካባቢው የሚመረቱ የበቆሎ፣ የቦሎቄና የበርበሬ ምርቶችን በቀላሉ ለገበያ ተደራሽ ለማድረግ ያስችላል ብለዋል።

የአካባቢውን ማኅበረሰብ በመሠረተ ልማት ተደራሽነት ተጠቃሚ ለማድረግ ፕሮጀክቱ ትልቅ ሚና እንዳለውም ገልጸዋል።

ኢንጂነር ገዛኸኝ አያይዘውም፤ በመንገድ ወሰን ክልል ውስጥ ያልተነሱ ንብረቶች፤ የውሀና የመብራት መስመሮች ፕሮጀክቱን በተያዘለት የግንባታ ቀነ ገደብ ለማጠናቀቅ ትልቅ ተግዳሮት እንደሆነባቸው ጠቁመው፤ ችግሩን ፈትቶ ፕሮጀክቱን በቀጣይ ዓመት ለማጠናቀቅ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል። ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ በትኩረት እየተሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የፕሮጀክቱ ሥራ ተቋራጭ የኪቢሻ ኮንስትራክሽን ኦፕሬሽን ማናጀር ኢንጂነር መለሰ ይልማ በበኩላቸው፤ ፕሮጀክቱ ከ878 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ጥራቱን በጠበቀ ደረጃ እየተሠራ ነው። መንገዱ ከ38 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን በገጠር 11 ሜትር በከተማ 21 ሜትር ስፋት ይኖረዋል ብለዋል።

እንደ ኢንጂነር መለሰ ገለጻ፤ ከ38 ኪሎ ሜትር በላይ የሚሸፍነው የቡልቡላ -አላጌ -ባራ - ሚቶ መንገድ ፕሮጀክት የአስፋልት ኮንክሪት ደረጃ በመገንባት ላይ ይገኛል። እየተገነባ ካለው ከ38 ነጥብ 8 ኪሎ ሜትሩ ውስጥ ዘጠኝ ኪሎ ሜትሩ አስፋልት ለብሷል፤ በ33 ኪሎ ሜትሩ ላይ አፈር ሙሌት ሥራ ተከናውኗል።

ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ሦስት ዓመት አስቆጥሯል ያሉት ኦፕሬሽን ማናጀር መሐንዲሱ፤ 28 ኪሎ ሜትሩ በተያዘው በጀት ዓመት የሚጠናቀቅ ሲሆን ቀሪው የመንገድ ግንባታ በመጪው ዓመት ሙሉ ለሙሉ ይጠናቀቃል ሲሉ ተናግረዋል።

በመንገድ ሥራው ከ500 እስከ 600 ለሚደርሱ የአካባቢው ማኅበረሰብ የሥራ ዕድል እንደተፈጠረላቸው ጠቁመው፤ ካሣ ለተከፈላቸው ቅድሚያ በመስጠት ተጠቃሚ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል።

የነዳጅ፣ የሲሚንቶ፣ የማሽነሪ አቅርቦትና የካሣ ክፍያ ችግሮች ለፕሮጀክቱ መጓተት ምክንያት መሆናቸውን ገልጸው፤ ችግሮቹን ፈትቶ መንገዱን ለማጠናቀቅ እየተሠራ ነው ብለዋል።

# የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኢንዱስትሪ በራሱ እንዲመራ የሚደረገው እንቅስቃሴ የሚያበረታታ ነው

ቃልኪዳን አሳዬ



አቶ ያሬድ ሞላ

አቶ ጌታቸው በሻወርድ

አዲስ አበባ፡- የብሔራዊ ባንክ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኢንዱስትሪ በራሱ እንዲመራ ለማድረግ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ የሚያበረታታ መሆኑን የኢትዮጵያ መድን ሰጭዎች ማኅበር አስታወቀ፡፡

ብሩህ ፋይናንስ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢንሹራንስ ሰርተፊኬት ያሠለጠናቸውን 79 ባለሙያዎች በትላንትናው ዕለት አስመርቋል።

በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ የኢትዮጵያ መድን ሰጭዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ያሬድ ሞላ እንደገለፁት፤ ብሔራዊ ባንክ ከዓለም ባንክና የተለያዩ የውጭ ባሙያዎችን ያቀፈ ቡድን በማዋቀር የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኢንዱስትሪ በራሱ እንዲመራ ለማድረግ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ የሚያበረታታ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የብሔራዊ ባንክ የኢንሹራንስ ዘርፉ ከአንድ ዓመት በኋላ እራሱን እንዲችል እንደሚደረግ መግለጹን ያነሱት አቶ ያሬድ፤ ይህ መሆኑም ለተገልጋዩ ማኅበረሰብና በዘርፉ ላሉ ሙያተኞች ምቹ አጋጣሚን የሚፈጥር ነው ብለዋል፡፡

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ ተመራቂዎቹ በኢትዮጵያ ከሚገኙ ከሁሉም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የተወጣጡ ሲሆን ይህም ለኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ኢንዱስትሪና ለመድን ሰጭዎች ማህበር ትልቅ አቅም የሚፈጥር ነው።

አቶ ያሬድ፤ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኢንዱስትሪ ብዙ ፈተናዎች እንዳሉት አንስተው፤ የኢንሹራንስን ጠቀሜታ ማኅበረሰቡ በሚገባ መረዳት ባለመቻሉ የግንዛቤ የማስጨበጡ ሥራ በስፋት መሥራት እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡

የዓለም የፋይናንስ ሥርዓት በከፍተኛ ሁኔታ እየተቀየረ መጥቷል፤ ከውድድሩ ላለመውጣትና ተወዳዳሪ በመሆን ውጤት ለማምጣት ትልቁ ግብዓት ብቃት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት ሲቻል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የብሩህ ፋይናንስ መሥራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ ጌታቸው በሻወርድ በበኩላቸው፤ በዘርፉ ላይ እየታየ ያለውን የተማረ የሰው ኃይል እጥረት ለመፍታት በኢንሹራንስና በባንኩ ዘርፍ በሀገር ውስጥና በውጭ ከሚገኙ የተለያዩ ተቋማት ጋር በጋራ እየሠራን ነው ብለዋል።

በቀጣይ በኢንሹራንስ ዘርፉ ላይ በኢትዮጵያ የማይሰጡ የተለያዩ የትምህርት መስኮችን ለመክፈት መታቀዱን ያነሱት አቶ ጌታቸው፤ ትምህርቱን በቀጣይ በድሬዳዋ፣ በሀዋሳና በሌሎችም ከተሞች የማስፋፋት ሥራ እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ጌታቸው ከሆነ፤ በተቋሙ የሚማሩ ተማሪዎችን በቀጣይ ወደተለያዩ ሀገራት በመውሰድ የሥራ ላይ ልምድ እንዲወስዱ ይደረጋል።እንዲሁም በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሀገራትም ትምህርት የማስፋፋት ሥራ ይሠራል፡፡

በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ የውጭ ባንኮች ሊገቡ እንደሆነና የካፒታል ገበያ መቋቋሙን የጠቆሙት ዋና ሥራ አስኪያጁ፤ ብሩህ ፋይናንስ በካፒታል ገበያ ዘርፍ ሁለት የትምህርት መስኮችን በመክፈት ተማሪዎችን እያስተማረ እንደሚገኝ አመልክተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕጋዊነትን በመምረጥ ራስንም፤ ቤተሰብንም ካላስፈላጊ መከራና ስቃይ መታደግ ይገባል!

ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር እንደ ሀገር ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል። በችግሩ ዙሪያ ዜጎች ተገቢውን ግንዛቤ መፍጠር ባለመቻላቸው አሁንም ብዙ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል። በመሆኑም ተገቢውን ግንዛቤ ማዳበር እስካልቻልን በቀጣይም የሀገር ፈተና ሆኖ መዝለቁ ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

ምክንያቱም በግጭቶች፣ በኑሮ ውድነት፤ ለራስ እና ለቤተሰብ የተሻለ ሕይወትን ከመሻት በሚመነጭ ጉጉት በሕገወጥ መንገድ በደላሎች ተታለው ድንበር ተሻግረው የሚሰደዱ ዜጎቻችን ቁጥር ዕለት ዕለት እየጨመረ ነው።

ይህ የሀገርን ክብር፣ የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች ችግር ውስጥ እየከተተ ያለ ዓለም አቀፍ ችግር በእኛ ሀገር መስተዋል ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል። በነዚህ ዓመታት ውስጥም በሕገወጥ ደላሎች ተወናብደው በረሀ የበላቸው፣ የባሕር ሲሳይ የሆኑ ዜጎቻችን ቁጥር ጥቂት የሚባል አይደለም ።

በአደባባይ በጽንፈኞች ሰለባ የሆኑ፣ የከፋ ሰብዓዊ ቀውስ ውስጥ የገቡ፤ ባልተገባ መልኩ ለእስርና እንግልት እንዲሁም ለግዞት የሚዳረጉ ዜጎቻችንን ቁጥርም ቢሆን በየእለቱ እያሸቀበ እንጂ እየቀነሰ ያለበት ሁኔታ አይስተዋልም ።

በተለይም ወደ አውሮፓ እና መካከለኛው ምሥራቅ ወዳሉ ሀገራት የተሻለ ኑሮ ፍለጋ የሚሰደዱ ዜጎቻችን፣ መንገዳቸው ሕጋዊነት የተላበሰ ካለመሆኑ በተጨማሪ፣ በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሠረተ ባለመሆን ብዙ ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍሉ ተገድደዋል።

ለተሻለ ሕይወት ፍለጋ የሚደረግ የሰዎች ድንበር ዘለል እንቅስቃሴ /የውጪ ሀገር የሥራ ስምሪት/ የተለመደ እና ዓለም አቀፍ ባሕሪ የተላበሰ ነው። በተለይም በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ዜጎች የተለመደ እና በመንግሥት ደረጃም የሚበረታታ ነው። ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገትም ትልቅ አቅም ተደርጎ የሚወሰድ ነው ።

ይህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ በአብዛኛው በሀገራት መንግሥታት መካከል በሚደረግ ሕጋዊ ስምምነት የሚመራ፤ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ለሚፈልሱ ሰዎች መሻት ስኬት መተማመኛ እና ማስተማመኛ ያለው ነው። እነዚህን ሰዎች ካላስፈላጊ እንግልት ፣ መከራ እና ስቃይ የሚታደግ ጭምር ነው።

ከሕጋዊነት ባለፈም ሥራ ፈላጊዎች ስለሚሄዱበት አካባቢ የተሻለ ግንዛቤ ኖሯቸው፤ በሚሄዱባቸው አካባቢ ካሉ ሕዝቦች ባሕል፣ ሃይማኖት እና ማኅበራዊ መስተጋብር ጋር የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችል ዝግጁነት መፍጠርን ታሳቢ ያደረገ ነው ።

የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ድንበር የሚሻገሩ ሰዎች ለሚሄዱባቸው አካባቢዎች ባይተዋር ሳይሆን፤ ፈጥነው ራሳቸውን ከአካባቢው ጋር እንዲያላምዱ የሚያስችል፣ በተሻለ እውቀት እና ክህሎት ተደግፈው ከድንበር ባሻገር ያለውን ተስፋቸውን የሚጨብጡበትን ዕድል የሚፈጥር ነው።

እነዚህ ሀገራት በዚህ መልኩ ለሥራ ከሚያሰማሯቸው ዜጎቻቸው ብዙ ቢሊዮን ዶላር እያገኙም ነው። አጋጣሚውን ለዜጎቻቸው የሕይወት ለውጥ እንደ አንድ ትልቅ እድል አድርገው በመውሰድ፣ ዕድሉን በአግባብ ለመጠቀም ተቀናጅተው በመሥራት ውጤታማ ሆነዋል።

በኛ ሀገር ያለው እውነታ ግን በዚህ ደረጃ የሚገለጽ አይደለም። ዜጎች የዚህ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በተለያዩ ወቅቶች ፤ የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም፤ ጥረቶቹ በሚመለከታቸው አካላት ቅንጅት ማነስና እና በሕዝቡ ውስጥ ባለው የግንዛቤ እጥረት የተጠበቀውን ያህል ውጤታማ ሳይሆን ቀርቷል።

በተለይም በሀገራችን ዘርፉ በአብዛኛው በሕገወጥ ደላሎች የሚዘወር መሆኑ፤ ችግሩ ከመቀነስ ይልቅ እየሰፋ ሄዷል ። በዚህም ዜጎቻችን ላልተገባ መከራ እና ስቃይ፤ ሞት እና የጤና ችግሮች እየተዳረጉ ነው። ችግሩ እንደ ሀገርም እየፈጠረ ያለው ስብራት በቀላሉ የሚታይ አይደለም ።

ዜጎቻችን የተሻለ ሕይወት ፍለጋ የሚያደርጉት ፍልሰት በመንገድ ከሚደርስባቸው እንግልት ባለፈ፤ በደረሱባቸው ሀገራት በሕገወጥ መንገድ መገኘታቸው፤ እንዲሁም ለአካባቢ ሕዝቦች ባሕል፣ ሃይማኖት እና ማኅበራዊ መስተጋብር ባይተዋር መሆናቸው ለተጨማሪ ችግሮች ዳርገዋቸዋል ።

ይህንን ሀገራዊ ችግር ለዘለቄታው ለመፍታት መንግሥት ለተሻለ ሕይወት ፍለጋ የሚደረግ የዜጎችን ፍልሰትን ሕጋዊ ወደ ሆነ የውጪ ሀገር የሥራ ስምሪት ለመለወጥ በስፋት እየተንቀሳቀሰ ነው። በተለይም ጉዳዩን አስመልክቶ ከመካከለኛናው ምስራቅ ሀገራት ጋር እያደረገ ያለው ውይይትና ውይይቶቹን ተከትሎ እየተደረሰባቸው ያሉ ስምምቶች የሚበረታቱ ናቸው።

ስምምነቶቹ ሕገወጥ ደላሎችን ከዘርፉ በማስወጣት፣ የውጪ ሀገር የሥራ ስምሪቶች ሕጋዊ እንዲሆኑ ከማስቻል ባሻገር፤ ዜጎች የተስፋቸው ባለቤት እንዲሆኑ መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር ነው፡፡ እነዚህ ዜጎች ራሳቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን ከዚያም አልፈው ሀገራቸውን የተሻለ ተጠቃሚ የሚያደርጉበትን ዕድልም የሚፈጥር ነው ።

ይህንን አሁናዊ እውነታ በአግባቡ በመረዳት ዜጎች ለሕልማቸው ስኬት፤ ሕጋዊ የሆነውን መንገድ በመከተል ራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን ሕገወጥነት ሊያስከትል ከሚችለው መከራ እና ስቃይ እንዲሁም አላስፈላጊ እንግልት መታደግ ይጠበቅባቸዋል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በዓባይ ግድብ የታየው ትብብር በሌሎች ዘርፎች ይደገም

ዓለማየሁ ግዛው

ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልፅግና የዜጎች አንድነትና ትብብር ዋነኛው መሣሪያ ነው:: ሀገር በሁሉም ነገር አድጋና ዘምና፣ ዓለም የደረሰበትን የሥልጣኔ ማማ መቆናጠጥ የምትችለው በሁሉም ዜጎች ፍላጎትና ጥረት መሆኑ አያጠያይቅም:: ብዙኃኑ የሚያልሙትና የሚመኙትን እድገትና ብልፅግና ለማምጣት ብዙ እንቅፋቶችን አልፎ እና በመተባበር አንድ ላይ ቆሞ መገኘት ደግሞ ለምርጫ የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም::

እንደ ሀገር የእድገትና ሥልጣኔ ማማውን ልንቆናጠጥ የምንችለው ጠንክሮ በመሥራትና የሚያጋጥሙትን መሰናክሎች በትብብር ክንድ ነቅለን በመጣል ነው:: ለዚህም የሠለጠነ ማኅበረሰብና በኢኮኖሚ የበለፀገችን ሀገር እውን ለማድረግ ዛሬ ላይ የሚታዩትን ፈተናዎችን ብስለት በተሞላበትና በአንድነት መሻገር ዋናውና አስፈላጊው ጉዳይ ነው::

ለዚህም ትልቅ ማሳያ ሊሆነን የሚችለው የተጋረጡብንን ችግሮች አልፈን የነገ እድገትና ሥልጣኔ ተስፋችን የሆነው የዓባይ ግድብን እውን ማድረጋችን ነው:: ግድቡ በ2003 ዓ.ም በቀድሞ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ የመሠረት ድንጋይ ተጥሎ ግንባታው ከጀመረ ጊዜ አንስቶ ሥራው ብዙ ፈተናዎች ተሻግሮ የአስራ ሦስት ዓመት ልደቱን ሻማ ለኩሷል::

የዓባይ ውሃ ዛሬ ላይ ለኢትዮጵያ እንዳለፉት ዘመናት «ላም አለኝ በሰማይ» አይደለም:: የሚታይ የሚጨበጥ የመጪው ትውልድ ጭምር አንጡራ ሀብት ሆናል:: እዚህ ደረጃ እስኪደርስ ግን ያለፈባቸው ፈተናዎች፣ የተሻገራቸው እንቅፋቶች ጥቂት አይደሉም:: ፈተናው ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ግድብ ገንብታ ዜጎቿን ከድህነት አረንቋ ለማውጣት ስትወጥን ከሚያስፈልገው ገንዘብ ይጀምራል::

የወንዙን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት የማይፈልጉና የኢትዮጵያ እድገትና ሥልጣኔ የሚያንገበግባቸው ሀገራትም ግንባታው ቀድሞ እንዳይጀመር ዓለም አቀፍ የገንዘብ ምንጮችን ጠርንፎ በመያዝ እንዲዘገይ የሚችሉትን ብቻ ሳይሆን የማይችሉትንም ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል:: እነዚህን ግዙፍ ፈተናዎች ግን ኢትዮጵያውያን ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ በአንድነትና በተባበረ ክንድ ቆመው ባደረጉት ሁለንተናዊ ድጋፍ ግድቡን በማይታመን መልኩ ለማጠናቀቅ ተቃርበዋል::

የቀደመው ትውልድ የራሱን ጥረት ቢያደርግም በነበረው ትልቅ ሴራ ግድቡ እንኳን ሊሠራ ሊታሰብ የማይቻል ይመስል ነበር:: ኢትዮጵያውያን አንድ በመሆን ግን የገንዘቡም ምንጭ፣ የምሕንድስናውም ሊቆች ራሳቸው ሆነው ግንባታውን በማስጀመር ለፍፃሜ አድርሰውታል:: የገንዘቡ ምንጭ እራሱ የሀገሬው ዜጋ በመሆን እያንዳንዱ ሰው አቅሙ በፈቀደ መጠን በማዋጣት ግድቡ አሁን ከደረሰበት ከፍታ ላይ እንዲቀመጥ አስችሎታል::

ኢትዮጵያውያን በመተባበር ዳግማዊ ዓድዋን በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ጉባ ተራሮች መሐል ለዘመናት ላይነቀል ሊተክሉ ችለዋል:: ይሄም እያስተማረን የሚገኘው ኢትዮጵያውያን በትብብርና በአንድነት ከቆሙ የበለፀገች ሀገርን መፍጠር እንደማይሳናቸው ነው::

የዓባይ ግድብ ኢትዮጵያን በብዙ መልኩ በብዙ ደረጃዎች ከፍ የሚያደርግና የኢትዮጵያውያን ሕይወት ለመሆን ቢቀርብም በብዙ አስቸጋሪና ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ አልፎ የምርቃት ባነሩን ለመቁረጥ እና የመላው ኢትዮጵያውያን የደስታ ምንጭ ሊሆን ጥቂት ነገሮች ቀርተውታል:: እስከ አሁን የተጓዘችባቸውን አስቸጋሪ ሁኔታዎችንም በትልቅ ድል በመወጣት ከአፍሪካ አልፎ በዓለም ደረጃ ታላቅ መሆናችንን የምናሳይበት ቀን እሩቅ አይሆንም::

ይህም ኢትዮጵያውያን በአንድነት ከቆሙና በመደማመጥ፣ በመከባበር፣ ሃሳብን በማዋጣት የሀገራቸው ግንባታ ላይ ካተኮሩ ዓለም የደረሰበት የሥልጣኔና የኢኮኖሚ ደረጃ መድረስ እንደሚችሉ የሚያረጋግጥ ነው:: ይህ በዓባይ ግድብ ላይ የታየው አንድነትና መተባበር በሌሎች ዘርፎችም ሊደገም ከቻለ የበለፀገች እና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ሀገርን መፍጠር እንደሚችሉ ማሳያ ነው::

የግድቡን ግንባታ ከዳር ለማድረስ የታየው ትብብርና ፈተናን የማሸነፍ ፅናት እንዲሁ ዝም ብሎ የተገኘ አይደለም:: ከዚህ ትልቅ ትምህርት ሊወሰድ ይገባል:: ካለፈተና የሚመጣ ውጤት አይኖርም:: ችግር ትልቅ ትምህርትንና መፍትሔን የሚሰጥ የመማሪያ መድረክም ነው:: ለዚህም በቂ ዝግጅት ማድረግና ወደፊት ለሚገጥሙን ችግሮችና እንቅፋቶች እንደየሁኔታው በቂ መፍትሔን መስጠትና በአሸናፊነት መወጣትን የምንማርበት ድል ሊሆን ይገባል::

የሚገጥሙንን እንቅፋቶች እንደመልካም አጋጣሚ መመልከት ነገ የሚገጥሙንንን ፈተናዎች ሳንሸበርና ሳንደናገጥ ተባብረን ለመሻገር ትልቅ የመንፈስ ስንቅ ይሆነናል:: አሁን ለገጠሙን እና እየገጠሙን ለሚገኙት የሠላም እጦት ድህነት እና ሌሎች ሀገራዊ ችግሮቻችንን አልፈን የበለፀገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ከዓባይ ግድብ ስኬታችን በላይ ምሳሌና አስተማሪ የለም::

**በዓባይ ግድብ ዙሪያ የተጋረጠብንን ችግርና ፈተና የተጋፈጥንበትን የትብብር መንፈስ በመከተል እና በሌሎች ዘርፎች ድልን በመቀዳጀት ለመጪው ትውልድ የምትመች ሀገር ማስረከብ ትልቁ የቤት ሥራችንም ሊሆን ይገባል**

በመሆኑም ግድቡ ተሻግሮ የመጣቸውን ተቆጥሮ የማያልቁ ችግሮችን እንደ ትምህርት በመውሰድ እና ችግሮችን ወደ ድል በመቀየር የምንመኛትን የበለጸገች አገር ለመፍጠር በሁሉም ዘርፎች በጋራ መቆምና መተባበር ዛሬም፣ ነገም፣ ወደፊትም ሊለየን ይገባም:: አሁን ካለንበት ችግር ለመውጣት ተስፋ የተጣለባቸውን እንደ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ያሉት ተቋማት የጀመሩትን ሥራ ከስኬት እንዲያደርሱ፣ የመተባበር አድማሳችንን በማጉላት ረገድ የሚጫወቱት ሚና የጎላ ነው::

እንደዚህ ዓይነት ተቋማትን በማብዛት የሃሳብ ልዕልና የሚያሸንፍበት ባሕል የምንገነባ ከሆነ የትብብር መንፈስን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ እንችላለን:: ሕዝብ ከተባበረ እና በአንድነት ከቆመ ሀገራችን በአጭር ጊዜ አድጋ ማየት እንችላለን::

በዓባይ ግድብ ዙሪያ የተጋረጠብንን ችግርና ፈተና የተጋፈጥንበትን የትብብር መንፈስ በመከተል እና በሌሎች ዘርፎች ድልን በመቀዳጀት ለመጪው ትውልድ የምትመች ሀገር ማስረከብ ትልቁ የቤት ሥራችንም ሊሆን ይገባል:: ሁላችንም እንደየእውቀታችንና ሙያችን በየዘርፉ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት የተቻለንን ጥረት ማድረግ ይገባል::

“ድር ቢያብር አንበሳ ያስር” የሚለውን የሀገሬውን ብሂል በመከተል ችግሮችን የሚያሸንፍ ሁለንተናዊ ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል:: እነዚህን ለውጦች ለማምጣት ከእያንዳንዳችን ምን ይጠበቃል የሚለውም ጥያቄ አብሮ መነሳት ይኖርበታል::

ለመተባበሩና በአንድነት ለመቆሙ መጀመሪያ መቅደም የሚኖርበት የኔ ድርሻ ምንድ ነው? የሚለውን ነገር ለይተን ስናውቅ ነው:: ሁሉም ለትብብሩ የአቅሙን የሚያዋጣውም ከዚህ ተነስቶ ይሆናል:: ለዚህም በማደግ ላይ ከሚገኙትና ካደጉት ሀገራት ልምድ በመውሰድ ለሀገር እድገትና ብልፅግና የድርሻችንን ማዋጣት ይኖርብናል::

ኢትዮጵያ ሠላም እና ፍትሕ የሰፈነባት ሀገር፣ በቴክኖሎጂ የበለፀገች፣ ዜጎቿ ከድህነት አረንቋ ተላቀው የሚኖሩበት ሀገር እንድትሆን በዓባይ ግድብ የታየው ትብብር እንዲደገም በየዘርፉ ባለን ሙያ የበኩላችንን ሚና ልንጫወት ይገባል::

ዜና

# በመዲናዋ በከተማ ግብርና ከ638 ሺህ በላይ ሰዎች እየተሳተፉ ነው

## -ከ11 ሺህ በላይ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ የከተማ ግብርና መርሐ ግብር 638 ሺህ 125 ሰዎች እየተሳተፉ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን አስታወቀ። በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ለ11 ሺህ 617 ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩም ተጠቁሟል።

የኮሚሽኑ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንድወሰን አካሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመዲናዋ በሚከናወነው የከተማ ግብርና መርሐ ግብር የተሳታፊና የተጠቃሚ ቁጥርን ለመጨመር እየተሠራ ይገኛል።

በመዲናዋ እየተከናወነ ባለው የተቀናጀ የከተማ ግብርና ሥራ በ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት በእንስሳት፣ አትክልት፣ ሰብልና ፍራፍሬ ልማት የተሰማሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ቁጥር 638 ሺህ 125 ደርሷል ብለዋል።

በከተማ ግብርና ተሳታፊና ተጠቃሚ ከሆኑት 638



ሺህ 125 የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል 455 ሺህ 272ቱ በነባር የቀጠሉ ሲሆን፤ 182 ሺህ 923ቱ ደግሞ በአዲስ የቤተሰብ ፍጆታ የተቀላቀሉ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

በከተማ ግብርና መርሐ ግብር ከግለሰብ አልፎ ማኅበራት፣ የግልና የመንግሥት ተቋማት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ እድሮች፣ ወረዳዎችና ክፍለ ከተማዎች ተጠቃሚና ተሳታፊ እንዲሆኑ እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ አንድ ሺህ 831 ተቋማትን በነባር ማስቀጠልና 456 ተቋማትን በአዲስ መልክ ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት በእንስሳትና እፅዋት ሀብት ልማት ለ15 ሺህ 710 ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ11 ሺህ 617 ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር የእቅዱን 70 በመቶ ማሳካት መቻሉን ተናግረዋል።

ኮሚሽኑ ነባር ተጠቃሚዎችን በማስቀጠል፣ አዲስ የቤተሰብ ፍጆታን ተጠቃሚ በማድረግ፣ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ችግኞችን በማሰራጨት ማኅበረሰቡ እና ተቋማት በከተማ ግብርና ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና ቀጣይነት እንዲኖረው በትኩረት እየሠራበት መሆኑን አብራርተዋል።

እንደ አቶ ወንድወሰን ገለጻ፣ በከተማ ግብርና መርሐግብር ተጠቃሚ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች በጓሮ አትክልትና በእንስሳት እርባታ የምግብ ፍጆታቸውን መሸፈን ችለዋል። የከተማው ነዋሪዎችም አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ እንቁላል፣ ወተት እና ሌሎች ምርቶችን በተመጣጠነ ዋጋ ማግኘት እንዲችሉና አቅርቦትን በማሳደግ ረገድ ውጤታማ መሆኑን አስረድተዋል።

የከተማ ግብርናንና የሌማት ትሩፋትን በተጠናከረ ሁኔታ ለማስቀጠል የተሳታፊ ቁጥርን የመጨመር፣ የከተማ ግብርናን የማዘመን፣ የነበሩ ድክመቶችን በመለየት ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ድክመቶችን ማረም፣ የግብዓትና የቴክኖሎጂ አቅርቦትን መጨመር፣ የድጋፍና ክትትል ሥራውን እስከታችኛው ደረጃ ማውረድ፣ ልምድና ተሞክሮዎችን መለዋወጥ የትኩረት አቅጣጫ መሆናቸውን አስገንዝበዋል።

## ለውጪ ገበያ ከቀረቡ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች የውጪ ንግድ 41 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 23 ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል።

በዘጠኝ ወሩ የተገኘው 23 ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ጫማ፣ ቦርሳ፣ የቆዳ ጓንት፣ ያለቀለትና በከፊል የተጠናቀቀ ቆዳን ለውጭ ሀገራት ገበያ በማቅረብ መሆኑን ገልጸው፤ ከቆዳ ፋብሪካ 15 ሚሊዮን ዶላር፣ ከጫማ ፋብሪካ አንድ ሚሊዮን ዶላር፣ ከጓንት ሦስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዶላር፣ ከቦርሳ ሁለት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት መቻሉን ጠቅሰዋል።

ቻይና፣ ኢንዶኔዢያ፣ ሕንድና ቬትናም ዋነኛ የኢትዮጵያ ቆዳ ውጤቶች መዳረሻ ሀገራት ሲሆኑ፤ ወደ አውሮፓና አሜሪካ የሚላከው የቆዳና ቆዳ ውጤት ምርት በተለያዩ ምክንያቶች ቀንሷል ብለዋል።

እንደ አቶ መሐመድ ገለጻ፣ በዘጠኝ ወሩ 41 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት የታቀደ ቢሆንም ማግኘት የተቻለው 23 ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር ብቻ ነው። የፋብሪካዎች በሙሉ አቅም አለማምረት፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ የገበያ መቀዝቀዝ፣ ጫማ ፋብሪካዎች በሀገር ውስጥ ገበያ ትኩረት ማድረጋቸው እና የአንዋ ማዕቀብ አፈጻጸሙ ደካማ እንዲሆን ምክንያት መሆናቸውን አስረድተዋል።

በዘርፉ ያሉትን ማነቆዎች ለመፍታት የ10 ዓመት የቆዳ ልማት ስትራቴጂ ተቀርጾ ወደ ተግባር የተገባ መሆኑን ገልጸው፤ የጥሬ ቆዳ ጥራትና አቅርቦትን የማሻሻል፣ የገበያ አማራጮችን የማስፋፋት፣ የግብዓት፣ የቴክኖሎጂ እና የፋይናንስ አቅርቦትን የማሻሻል ሥራ በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ እቅድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እንደሚሠራ ተናግረዋል።

አምራች ፋብሪካዎች በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን በሀገር ውስጥ ገበያ ራሳቸውን ማብቃት ተገቢ ነው ያሉት አቶ መሐመድ፤ በቴክኖሎጂ፣ በዲዛይን፣ በፋሽን እና በምርት ልማት ድጋፍ በማድረግ በጥራትና በብዛት እንዲያመርቱ፣ በሀገር ውስጥ ገበያው እንዲጠቀሙ እና በዓለም አቀፍ ገበያው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ ይሠራል ብለዋል።

በሙሉ አቅማቸው የማያመርቱ ፋብሪካዎች የሀገር



ውስጥ ገበያን ተጠቅመው እንዲንቀሳቀሱ የማድረግ ሥራ መሠራቱን የገለጹት አቶ መሐመድ፤ በቀጣይም በተጠናከረ ሁኔታ አምርተው ወደ ውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

አምራች ፋብሪካዎች እርስ በእርሳቸው በገበያ የማስተሳሰር፣ ገበያ የማፈላለግ፣ በቆዳ ኢንዱስትሪው የሚሳተፉ የተለያዩ ባለሀብቶች፣ ባለሙያዎች እንዲሁም ሸማቾችን በማገናኘት ዘርፉ እንዲነቃቃ ጥረት ይደረጋል ሲሉ አስታውቀዋል።

## ‹‹ኢትዮጵያን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ጉራጌ ስለ ሰላም የሚያስተምርና በሰላም የሚኖር ምሳሌ የሆነ ሕዝብ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያን ለመከፋፈልና ለማጋጨት ገንዘባቸውን፣ እውቀታቸውንና ጊዜቸውን በመስጠት በየዕለቱ ብዙ የሚጥሩ መኖራቸውን ጠቅሰው፤ ጉራጌ ‹‹አንድነት ኃይል ነው›› ብሎ ያምናል፡፡ ከዚህም ኢትዮጵያውያን ሊማሩ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ስለሠላም ሳናስብ፣ ሳንኖርና ሳንናገር ሠላምን ልንጎናጸፍ አንችልም ያሉት ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፤ ኢትዮጵያን ሠላምን አብዝቶ መፈለግ፣ በአብሮነት በመኖር የበለፀገችና ለሁሉ የምትመች ሀገር ለማየት ልንሠራ ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ጊዜ የወራሪዎችን ሙከራ የመከተችና ቅኝ ያልተገዛች ሀገር መሆኗን አውስተው፥ ሆኖም ኢኮኖሚያዊ ነፃነቷን ሳታረጋግጥ መቆየቷን አንስተዋል።

የጉራጌ ሕዝብ በንግድ ዘርፍ ያሳዩት ውጤትም ኢትዮጵያን ከኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት ለማላቀቅ አብነት መሆኑን ጠቅሰው፤ መላው ኢትዮጵያውያን ለልማትና ብልፅግና መቆም እንዳለባቸው አመልክተዋል።

ኢትዮጵያውያን ብዙ የማንነት መገለጫ እንዳላቸው መቀበል እንደሚገባቸው ጠቅሰው፤ የባሕል፣ የቋንቋ፣ የአካባቢ አቀማመጥ ልዩነት ሀገር የሚበትን መሆን እንደሌለበት ገልጸዋል።

ጉራጌ ስለሠላም የሚያስተምርና በሠላም የሚኖር ሠላምን የሚያስተጋባ ሕዝብ መሆኑን በመግለፅ፤ በተለይም በውስጡ የተለያዩ ማንነቶች ቢኖሩትም በጉራጌነት አንድ ሆኖ በመኖር የኢትዮጵያ አንድነት ምሳሌና ምልክት ሆኖ መኖሩን ተናግረዋል።

ከልመና ለመውጣት፣ ቁጠባን ለማዳበር፣ ንግድን ለማስፋፋት በአንድነት መረባረብ ወሳኝ መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ታታሪው የጉራጌ ሕዝብ ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ ትበለፅጋለች የሚል ፅኑ አቋም ይዞ ከመንግሥት ጎን ሊቆም ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የምትበለጸገው በብርቱ ጥረት መሆኑን ገልፀው፤ ሀገርን ለመከፋፈልና ለማጋጨት የሚሞክሩ ኃይሎችን ቅዠት ለማክሸፍ አንድነትን ማጠናከር ወሳኝ እንደሆነ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያን በብርቱ ጥረት ወደ ብልፅግና ከፍታ በመውሰድ የአፍሪካ የነፃነትና የብልፅግና ተምሳሌት ለማድረግ መትጋትን መርጠናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ መላው ኢትዮጵያውያንም ለዚህ ሀገራዊ ኃላፊነት በጋራ መቆም እንዳለባቸው ጥሪ አቅርበዋል።

## በአማራ ክልል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እስከ አሁን ከአንድ ነጥብ 6 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ደርሷል።

ቢሮው የ2016/2017 የመኸር ምርት የሰብል ልማት ከአምናው የተሻሻሉ አሠራሮችን በመተግበር የተሻለ ምርት ለመሰብሰብ አቅዶ እየሠራ ነው ያሉት ማንደፍሮ አስናቀ (ዶ/ር)፤ ይህም የማዳበሪያ፣ የምርጥ ዘር እና ለእርሻ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ከወዲሁ በማቅረብ ነው ብለዋል።

በባለፈው ዓመት የመኸር ወቅት በክልሉ 145 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ተገኝቷል ያሉት ማንደፍሮ አስናቀ (ዶ/ር)፤ ዘንድሮ ከአምስት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በማረስ 169 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት እየተሠራ ነው። ይህም የ24 ሚሊዮን ኩንታል ጭማሪ ያለው ሲሆን በሄክታር 63 ሺህ ነው ብለዋል።

ለዚህም የልማት ንቅናቄዎችን የማከናወን፣ ግብዓቶችን በፍጥነት የማቅረብ፣ የኩታ ገጠም አሠራርን የማጠናከር፣ ለባለሙያዎች ቴክኒካል ሥልጠና የመስጠት እና አርሶ አደሩ የምክር አገልግሎት እንዲያገኝ ተደርጓል ያሉት ማንደፍሮ አስናቀ (ዶ/ር)፤ በክልሉ የአንደኛ፣ የሁለተኛ እና የሦስተኛ የእርሻ ሥራ መጀመሩን ገልጸዋል።

በዚህም በመጀመሪያው ዙር የእርሻ ሥራ ሁለት ሚሊዮን 400 ሺህ ሄክታር የሚጠጋ መሬት የታረሰ ሲሆን በሁለተኛ ዙር የእርሻ ሥራ አንድ ሚሊዮን 255 ሺህ ሄክታር መሬት ታርሷል ያሉት ማንደፍሮ አስናቀ (ዶ/ር)፤ በሦስተኛ ዙር የእርሻ ሥራ 435 ሺህ 200 ሄክታር መሬት መታረሱን ነው የገለጹት።

እንደ ማንደፍሮ አስናቀ (ዶ/ር) ገለፃ፤ አምና ከማዳበሪያ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የዋጋ፣ የእጥረትና መሰል ችግሮች ተከስተዋል። ዘንድሮ ከአምናው በመማር ከስምንት ሚሊዮን በላይ ኩንታል ማዳበሪያ ተገዝቷል። ይህም አምና ከተገዛው ጋር ሲነፃጸር ከሦስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ጭማሪ አለው።

ይህም ለአርሶ አደሮች እየተሰራጨ ይገኛል። እስከ አሁን ከአንድ ነጥብ 6 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ተሰራጭቷል ያሉት ማንደፍሮ አስናቀ (ዶ/ር)፤ ለመኸር ወቅት ከ185 ሺህ ኩንታል በላይ ምርጥ ዘር ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ እንደሆነም ጠቅሰዋል።

## የኤች ኤይ ቪ/ኤድስ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ያደታ ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ ቫይረሱ ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ ከተረጋገጠ ጊዜ ጀምሮ ግንዛቤ በመፍጠር ረገድ በርካታ እንቅስቃሴዎች ሲከናወኑ ቆይቷል።

ለዚህም መንግሥት የተለያዩ በሀገር ውስጥ ባለ ድርሻ አካላትንና ኅብረተሰቡን እንዲሁም ተራድዖ ድርጅቶችን በማሳተፍ በርካታ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል ያሉት አቶ ፍቃዱ፤ በእነዚህ ተግባራት አበረታች ለውጥ ማስመዝገብ በመቻሉ የስርጭቱን መጠን ከአንድ በመቶ በታች ለማድረስ ችሏል ብለዋል።

ነገር ግን በ2030 በታቀደው እቅድና ለዓለም መንግሥታትም በተገባው ቃል መሠረት የማኅበረሰብ የጤና ችግር ወደማይሆንበት ደረጃ የማድረሱን ሥራ፤ ማለትም የሞትና በአዲስ መያዝን ዝቅ እናደርጋለን የሚለውን ለማሳካት አሁንም ብዙ ሥራ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል፡፡

ይህን ለማሳካት በተሠሩ ሥራዎች ቫይረሱ በደማቸው ያሉ እንደ ከዚህ ቀደሙ በሕመም ሲሰቃዩና ሲቸገሩ ወይንም በፍጥነት ሲሞቱ አይታይም ያሉት አቶ ፍቃዱ፤ ማግለልና አድልዎም በጥሩ ሁኔታ ሊስተካከል በመቻሉ እንደማንኛውም ዜጋ አምራች እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል ብለዋል። የቫይረሱን ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ሁኔታም በበቂ ደረጃ ለውጥ ለማምጣት መቻሉ ቫይረሱ እንደ ከዚህ ቀደሙ እንዳይፈራ አድርጎታል ብለዋል።

ይሁን እንጂ እነዚህ ለውጦች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መዘናጋትን ፈጥረዋል ያሉት ኃላፊው፤ የሚዲያዎች ተሳትፎም ተቀዛቅዟል ሲሉ ጠቁመዋል።

በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት ኤች አይ ቪ ቫይረስን በተመለከተ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ትኩረት የሚሹና በይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ ብቻ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። እነዚህም ሴተኛ አዳሪዎች፣ አደንዛዥ እፅ የሚጠቀሙ ሰዎች፣ የረጅም ርቀት አሽከርካሪዎች፣ አፍላ ወጣቶች በተለይ (ከማኅበራዊ ሚዲያ ጋር በተያያዘ)፣ የቀን ሠራተኞች፣ ከማኅበራዊ ችግሮች ጋር ተያይዞ ተጋላጭ ናቸው ብለዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የስርጭት መጠኑ ከአንድ በመቶ በላይ ቢሆንም ከቦታ ቦታ በፆታ፣ በኅብረተሰብ ክፍል፣ በገጠርና በከተማ ከፍተኛ ልዩነት ያለው ነው ያሉት አቶ ፍቃዱ፤ በከተሞች ያለው ስርጭት በገጠር ካለው በሰባት እጥፍ እንደሚበልጥም ጠቁመዋል፡፡ ይህንን ልዩነት መሠረት ያደረገ አጠቃላይ ማኅበረሰቡን ተደራሽ የሚያደርግ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ እየተከናወነ አለመሆኑንም አብራርተዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የመጠጥ፣ የጫት ቤቶችና በሺሻ ቤቶች መስፋፋትም ሌላ ተግዳሮቶች እየሆኑ መጥተዋል። አንዳንድ ወጣት ሴቶች ከቫይረሱ በላይ እርግዝናን ይፈራሉ። የወጣቶች አዲስ የመያዝ ምጣኔ ጨመረ ባይባልም እየቀነሰ አይደለም፤ ይህ በራሱ ችግር ለመኖሩ አመላካች ነው ብለዋል።

ይህም በተለይ በወጣቶች በኩል ሁሉን አቀፍ ሥራ ባለመሠራቱ ዋጋ ሊያስከፍሉን የሚችሉ አጋላጭ ባሕሪያት እየተስተዋሉ መሆኑን ጠቁመው፤ በመሆኑም የኤች አይ ቪ ቫይረስን በተመለከተ ጠንካራ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እንደሀገር ማከናወን እንደሚጠበቅ ገልጸዋል።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## በቀጣናው ጂኦፖለቲካ ላይ ህያው አሻራውን ትቶ ያለፈው ሾተላዩ ሰላይ

ባለፈው ማክሰኞ ረፋድ ላይ በFB መንደር ስባዝን አንድ መርዶ ተመለከትሁ። መቼም በዚህ መንደር የታየው ሁሉ አይታመንም። ለማረጋገጥ ወደ አንድ አብሮ አደጌና ጓደኛዬ ሀሎ አልሁ። በማለዳው ስለተመለከትሁት መርዶ ሳረዳው እሱም እንደኔ ደንግጦ አለመስማቱን ነግሮኝ አጣርቼ ልደውልልህ ብሎኝ ተለያየን። እኔም መርዶውን ሟርት ያድርገው ብዬ እየተመኘሁ ወደ FB መንደር ተመልሰሁ። መርዶውን የሚያረጋግጡ መረጃዎች በስፋት እየተዘዋወሩ ስለሆነ ምኞቴ ከንቱ መቅረቱን ተረዳሁ።

ያ ልጆች ሆነን ፍኖተ ሰላም ላይ ጀብዱን ጉብዝናውና ትህትናው እንደ ዳዊት ተደጋግሞ እየሰማን ያሳደገን አርዓያችን፣ዝነኛችን/ሌጀንዳሪ/እና ምሳሌያችን የሆነው አምባሳደር ኮሎኔል አስማማው ቀለሙ 60 ዓመታትን ሌት ተቀን በታማኝነት በፍጹም ፍቅር ያገለገላትንና የሚወዳትን ሀገር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተለይቷታል። አሁንም ያየሁትን ማመን ቢቸግረኝ ወደ 8ኛ ክፍል የእንግሊዘኛ መምህሬ ጋሽ ዘላለም ልየው(Phd)ሀሎ አልሁ ገና ሀሎ ሲለኝ ያ የምሥራቅ አፍሪካን ጂኦፖለቲካ እንደ አዲስ የበየነው ሾተላዩ ሰላይ ማረፉ ታወቀኝ።

እንዳለመታደል ሆኖ እንጂ የአምባሳደር ኮሎኔል አስማማው ሞት በመደበኛው ሚዲያ በሰበር ሊነገር የሚገባው ነበር። በሞቱ አዘንሁ። መልሼ ደግሞ ተጽናናሁ። ለሀገሩና ለወገኑ ባበረከተው ዘመንና ትውልድ ተሻጋሪ ስራው ስሙን ከመቃብር በላይ ከፍ አድርጎ ስለሰቀለው አልሞተም ብዬ ተጽናናሁ።ጋሼ ፕሮፌሰር ዘላለም ልየው ደግሞ ሀገር ግዙፍ ተንቀሳቃሽ ቤተ መጽሐፍት አጣች ሲል ቁጭቱን ገለጸልኝ። እውነት ነው። አምባሳደር የቀጣናው ድክመት እንበለው ህመም መፍትሔ አልያም ፈውስ በእጁ ነበር። በልኩ ሳንጠቀምበት አመለጠን እንጂ።

አምባሳደር ኮሎኔል አስማማው ዝናን ያተረፈ/ሌጀንደሪ/ቢሆን ሲበዛ ትሁትና ቅን ነበር። ጓደኛዬ አዳሙ አንለይ ነው ሀዋሳ ላይ ከ20 ዓመት በፊት ከአምባሳደር ጋር ያስተዋወቀኝ። በእርግጥ ኮሎኔል አስማማው በአካል ባላውቀውም በስምና በዝና አውቀው ነበር። ሀዋሳ ላይ ስተዋወቀው ግን ያን ሁሉ ገድልና ዝና ተሸክሞ ግን ሲበዛ ትሁት ሆኖ ስመለከተው ለራሴ ገረመኝ። እንደገና እንደ አዲስ አከበርሁት። የታላቁ ዲፕሎማትና የደህንነት ሰው ታሪክ ዳጎስ ዳጎስ ያሉ መጽሐፍት ቢወጣውም ፤ ከተለያዩ ምንጮች የቀራረምሁትን ነው እያጋራኋችሁ ያለሁት። ቤተሰቦቹ አልያም የትምህርትና የምርምር ተቋማት ወይም የሚመለከተው የመንግሥት ተቋም ኮሎኔል አስማማው የህይወት ታሪክ እና ሀገራዊ አስተዋጾዎችን በመጽሐፍ መልክ ሰንደው ለትውልድም ለታሪክም ያቆዩታል ብዬ አምናለሁ።

ታላቋን ሶማሊያ ለመመስረት ኢትዮጵያን ለማፍረስና ለመበታተን ሌት ተቀን ይሰራ የነበረውን የሳያድባሬን መንግሥት በመጣልና ሀገሪቱ ዛሬ ድረስ እንዳትረጋጋ ያደረገውን እርሾ በመጣል ፤ሱዳን ሻእቢያንና ወያኔን በማስታጠቅ ሀገራችንን እንዳዳከመችው ሁሉ ፤ ብድር በምድር እንዲሉ የደቡብ ሱዳንን አማጽያን በማደራጀትና በማሰልጠን እንዲገነጠሉ በማድረግና ሱዳንን በማዳከም ኮሎኔል አስማማው የአንበሳውን ድርሻ ተጫውቷል። በድህረ ደርግ የሽግግር መንግስቱ ከገዛ ዜጋው ይልቅ ለሶማሊያ ተቆርቁሮ ሶማሊያን በመበተን እና የሶማሊያን ሕዝብ በማጎሳቆል ወንጅሎ ለ12 ዓመታት አስሮታል። በወቅቱ ይህ ውንጀላ ብዙ ያወዛግብና ያነጋግር ነበር።

በቀድሞው ጎጃም ጠቅላይ ግዛት ቆላ ደጋ ዳሞት የተወለደው ዶ/ር ቀለሙ የአርበኛ ቤተሰብ ልጅ መሆኑን ይናገራል:: አያቱ ፊታውራሪ ዓለማየሁ አጋዴን መሞታቸውን፣ አባቱ በጣሊያን ወረራ ተምጫ ሽለቆ ሦስት ሺህ ጦር ይዘው ከጠላት ጋር የተዋጉ አርበኛ እንደነበሩ ያስረዳል:: ‹‹አባታችን የቤተክህነት ትምህርት ስለነበረው ከገጠር ወደ ከተማ ገብተው በገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ ማገልገል ሲጀምሩ እኛም ተማርን:: ከስምንት ልጆች አሁን የቀረነው አራት ነን፣ ሆኖም ሁላችንም በትምህርት ብዙ ገፍተናል:: በቤተሰባችን ብዙ የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚዎች አሉ፤››በማለት ስለቤተሰቡ ያወጋል::

> **በዝግጅቱ ላይ የነበሩት የሥራ ጓዶቻቸው ሲያመሰግኗቸውና ሲያሞኳሿቸው ስናይ በፊትም ከምናውቀው በላይ ለሙያቸው የተሰጡና በዚህም ለሀገራችን ኢትዮጵያ ታላቅ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ገባን**

አምባሳደር ኮሎኔል አስማማውን ያወቀ ሁሉ በአፍታ ስለሚቀራረብ ከቤተሰቡ እንደ አንዱ ስለሚቆጠር ነው እስካሁን አንተ ያልሁት። እሱም የሚወደው ስለነበር። በተረፈ በእድሜም ሆነ ለሀገር በዋለው ውለታ አንቱ ቢባል ያንስበታል እንጂ አይበዛበትም። የመጀመሪያ ዲግሪውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ ማግኘቱን፣ ማኔጅመንት ተምሮ በዲግሪ መመረቁን፣ ወደ እስራኤል አቅንቶ በሪሶርስ አሎኬሽን ዘርፍ ከቤንጎሪዮን ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ ትምህርት መከታተሉንና በኢንተርናሽናል ሎው ሌላ የማስተርስ ዲግሪ መቀበሉን ይገልጻል::

በሆርቲካልቸር ቢኤስሲ ዲግሪ፣ ከዚያም ወደ ቡልጋሪያ በማምራት ከካርል ማርክስ ዩኒቨርሲቲ ሦስተኛ (ዶክትሬት) ዲግሪውን ሠርቷል:: ከለንደን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ የፖስት ዶክቶራል ፕሮግራም መከታተሉን፣ ከቀለም ትምህርቱ እኩል በወታደራዊ ሳይንስ ዘርፍም ብዙ ዓይነት ትምህርቶች መቅሰሙን ይናገራል:: በፖሊስ ሳይንስ በአድቫንስድ ዲፕሎማ በመጀመሪያ መመረቁንና የፖሊስ መኮንን ለመሆን መብቃቱን ያወሳል::

በትምህርት ላይ ትምህርት፣ በማዕረግ ላይ ማዕረግ እያከለ በሒደት እስከ ኮሎኔል ማዕረግ የደረሰው አንጋፋው ምሁር ወደ ደኅንነት ተቋምም ገብቶ በብዙ የኃላፊነት ደረጃዎች መሥራቱን አስረድቷል:: ‹‹የደኅንነቱን ዕቅድ (ፕላኒንግ) ዘርፍ መርቻለሁ፣ የኦፕሬሽን ሥራዎች ላይ ተሰማርቻለሁ፣ በምክትል ሚኒስትርነትም አገልግያለሁ፤›› ይላል። ለሦስት ዓመታት በሶማሊያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ነበር:: ስታር አምባሳደር ከመባል ባለፈ በሶማሊያ የተማረኩ የኢትዮጵያ ዜጎችን በልዩ ኦፕሬሽን ለማስለቀቅ የተወጣው የስድስት ወራት ዘመቻ ለብቻው ረጅም ታሪክ ያለው ነው ሲልም ይደመጣል:: በሌሎች ሀገሮችም ልዩ የስለላ ተልዕኮዎችን ሲወጣ መቆየቱን፣ በሀገር ጉዳይና በመንግሥት አስተዳደር ዘርፍ ያካበተው ዕውቀት ሰፊ መሆኑንም ይጠቅሳል::

የቀድሞው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሌተናል ኮሎኔል ብርሃኑ ባየህ ‹‹ያልታሰበው የሕይወቴ ፈታኝ ጉዞ እና የኢትዮጵያ አብዮት ተሳትፎዬ›› በተሰኘው ግዙፍ መጽሐፋቸው ስለ ኮሎኔል አስማማው ሰብእና እንዲህ ከትበዋል:: ‹‹በጣም ጎበዝ፣ ታታሪ፣ አዲስ ሃሳብ አፍላቂ ብቻ ሳይሆን ወዲያው በተግባር የሚተረጉም እንደሆነ አስመስክሯል:: ሠርቶ አይደክመውም:: በጣም ትጉ ነው:: በዚህም ምክንያት አለቆቹ ያደንቁታል:: በመሆኑም መንግሥቱ ሳይቀር አውቆታል::

አምባሳደር የኮሎኔል አስማማውን የሶማሊያ አምባሳደር እንዲሆኑ ማሰባቸውን ለርዕሰ ብሔሩ ሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ሲነግሯቸው “ጥሩ ምርጫ ነው::” በጣም ጎበዝ ልጅ ነው:: ማደግ የሚገባው ልጅ ነው:: ለእርሱ ተብሎ ሳይሆን ለሥራው:: ምንም ሥራ ይሰጠው ከሚጠበቀው በላይ ነው የሚፈጽመው:: እኔ እንኳን ለሌላ ሥራ ነው አስቤው የነበረው:: ጓድ ተስፋዬን የሚተካ እሱ እንዲሆን ነው...:: ብለዋቸዋል::

የአምባሳደር የኮሎኔል አስማማው ጠንቃቃነት የሚያሳይ አንድ ሰበዝንም ኮሎኔል ብርሃኑ እንዲህ መዘዋል:: ‹‹የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንደሆንኩ ዶክተር አስማማው ወደ ቢሮዬ ብቅ ብሎ ነበር:: በወቅቱ አንዲት የኤሌክትሪክ መሣሪያ ይዞ ነበር:: ትንሽ እንደተነጋገርን የቢሮዬ ግድግዳ ጣሪያ በመሣሪያዋ መረመረው:: የተደበቀ የድምፅ መቅረጫ ወይም ሌላ ነገር አለመኖሩን ለማረጋገጥ:: ፍተሻውን ሲጨርስ፤ ‹ምንም ነገር የለም ነፃ ነው፤› አለኝ:: እኔ ሳልጠይቀው ራሱ አስቦ የምናገረው፣ የምወያየው የምወስነው የምሰጠው ትዕዛዝ በሌላ እጅ እንዳይወድቅ፤ ምናልባትም በጠላት ሰላዮች እጅ እንዳይወድቅ ይኽን በማድረጉ ውለታውን አልረሳውም::››

በኢትዮጵያ ሦስት መንግሥታት ከ1950ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በፖሊስ፣ በመረጃና ደኅንነት ዘርፍ ሀገራዊና ሙያዊ አገልግሎትን አስማምተው ለስድስት አሠርታት ያክል ሠርተዋል ይለናል የአማርኛው ሪፖርተር በማስከተል:: ሀገራዊ የደኅንነቱን ዕቅድ (ፕላኒንግ) ዘርፍን በመምራት፣ ድንበር ተሻጋሪ የኦፕሬሽን ሥራዎች ላይ በመሰማራትም ተጠቃሽ ናቸው:: የፖሊስ ኮሎኔሉ አስማማው ቀለሙ:: በቀለሙም (በአካዴሚያ) እስከ ዱክትርና ዘልቀዋል::

ገጸ ታሪካቸው እንደሚያሳየው፣ በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ከሀገር ግዛት ሚኒስቴር እስከ ዘመነ ደርግ (ኢሕዲሪ) ከደኅንነት ሚኒስቴር ቀጥሎም የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር እስከ ምክትል ሚኒስትርነት የደረሰው የኮሎኔል አስማማው አገልግሎት፣ የኢትዮጵያን መልክዓ ምድራዊ ስትራቴጂካዊ ጥቅም ለማስጠበቅ እልህ አስጨራሽ ትግል በማድረግ የታወቀ ነው ሲል ጋዜጠኛ ሔኖክ በሪፖርተር ባስነበበን መጣጥፍ ይዘክራል::

በ1960ዎቹ መጨረሻና በ70ዎቹ መጀመሪያ ከሶማሊያ ጋር በነበረው ጦርነት የተማረኩ ኢትዮጵያውያንን በልዩ ኦፕሬሽን ለማስለቀቅ የተወጡት የስድስት ወራት ዘመቻ ስማቸውን በግዙፍ ያነሳዋል:: በሁለቱ ሀገሮች መካከል ሰላም ከሰፈነ በኋላ፣ ቀደም ሲል ‹‹ፔድሮ›› ተብለው በሞዛምቢካዊ ጋዜጠኛነት በሰለሏት ሶማሊያ የመጀመሪያው ባለሙሉሥልጣን አምባሳደርነት አገልግለዋል::

የኢትዮጵያ አብዮት እንደፈነዳ (1966) የፖሊስ መቶ አለቃ ሆነው በሕዝብ ደኅንነት ጥበቃ ውስጥ የሠሩት አምባሳደር ኮሎኔል አስማማው ፤ የፖሊስ ሳይንስን የተማሩት በአባዲና ፖሊስ ኮሌጅ በ9ኛው ኮርስ ሲሆን፤ በመቶ አለቅነት በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተመረቁት ታኅሣሥ 14 ቀን 1961 ዓ.ም. ነበር:: የመረጃና ደኅንነት ሙያን በይበልጥ ለማጠናከር ይረዳቸው ዘንድ በተለያዩ ሀገሮች በተለይም በእስራኤልና በጀርመን ሠልጥነዋል::

ሁለንተናዊ ዕውቀታቸውን ለትውልዱ ለማስረፅም ይረዳ ዘንድ የኮተቤ የደኅንነት ትምህርት ቤትን በመመሥረትና በኃላፊነት በመምራት ከመሥራታቸው በተጨማሪ በ1974 ዓ.ም. የስትራቴጂክ ጥናት ኢንስቲትዩትን በማቋቋም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ይወሳል:: ድኅረ ደርግ በሽግግር መንግሥቱ (በኋላ ኢፌዴሪ) ለ12 ዓመታት ያለክስ፣ ያለፍርድ የታሰሩት ኮሎኔል አስማማው፣ እስረኞች እንዲማሩ፣ ትምህርቱም በዚያው እንዲስፋፋ ማድረጋቸው ይገለጻል:: የ2010 ዓ.ም ለውጥን ተከትሎ በብሔራዊ ደኅንነት ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት አገልግለዋል:: በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ተጋባዥ ሌክቸረርም ነበሩ::

የጤና መታወክ እስካጋጠማቸው ታኅሣሥ 2016 ዓ.ም. ድረስ በብሔራዊ ደኅንነት ዩኒቨርሲቲ ሲያስተምሩ የቆዩት አምባሳደር ኮሎኔል አስማማው፤ በተወለዱ በ84 ዓመታቸው ያረፉት ቅዳሜ ሚያዝያ 5 ቀን 2016 ዓ.ም ሲሆን፤ ሥርዓተ ቀብራቸው በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የተፈጸመው ማክሰኞ ሚያዝያ 8 ቀን ነው:: ዜና ዕረፍታቸውን ተከትሎ የሐዘን መግለጫውን ያስተላለፈው የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት፣ ኮሎኔል አስማማው ቀለሙ ከ1956 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና ደኅንነት በማስጠበቅ ለ60 ዓመታት ያህል በመረጃና ደኅንነት ዘርፍ ሰፊ አበርክቶት አድርገዋል ብሏል::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰላምና ደኅንነት ጥናት ተቋም በተጋባዥ መምህርነት (ገስት ሌክቸረር) ያገለገሉት አስማማው ቀለሙ (ዶ/ር) ኅልፈትን ተከትሎ ተቋሙ ለሪፖርተር በላከው መግለጫው እንዲህ አለ፦ ‹‹አምባሳደር ዶ/ር አስማማው ቀለሙን ቀርቦ ከሕይወትና ከሥራ ልምዳቸው ለመማር በሰላምና ደኅንነት ጥናት ተቋም የምንገኝ መምህራን የወሰንነው የአቶ በላይ ገብረ ጻድቅ መጽሐፍ (‹‹የመረጃና ደኅንነት ሙያና የኢትዮጵያ ገጽታ››) በ2014 በተመረቀበት ዕለት ነው::

በዝግጅቱ ላይ የነበሩት የሥራ ጓዶቻቸው ሲያመሰግኗቸውና ሲያሞኳሿቸው ስናይ በፊትም ከምናውቀው በላይ ለሙያቸው የተሰጡና በዚህም ለሀገራችን ኢትዮጵያ ታላቅ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ገባን:: ‹‹ከስልክና የመጀመሪያ የዝግጅት ውይይቶች በኋላ በአራት ወራት ውስጥ ለ17 ቀናት ከ1፡30 እስከ 2፡00 ሰዓት የፈጁ ቃለ መጠይቆች አድርገንላቸዋል:: በኋላም ለድኅረ ምረቃ ተማሪዎቻችን ገስት ሌክቸረር ሆነው አገልግለዋል:: በመጨረሻም የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ የተገኘበት ፐብሊክ ሌክቸር አዘጋጅተንላቸዋል::

ከዚህ ሁሉ ምን ተማርን ምንስ አገኘን ከተባለ አንድ፡- ከልጅነት እስከ እስር ቤት የዘለቀ አዲስ ነገር ለመማር ለመፍጠርና ቁልፍ ተግባሮችን ለመሥራት በጥናትና ሙከራ ላይ የተመሠረተ መጋፈጥና በግል ተነሳሽነት ታላላቅ ሃሳቦችን መጀመርና ለፍሬ ማብቃት፤ሁለት፡-ሀገርን ከምንም ነገር አስቀድመው በሙያቸው ያካበቱትን ያላቸውን ሁሉ መስጠትና ማገልገል፤ሶስት፡- በጣም ውሱን የሆነ የሀብት መሠረትና ያልተመቻቸ ሁኔታ ላይ ሆኖም ቢሆን ተቋም መገንባትና ማጠናከር ላይ ትኩረት መስጠት፤አራት፡- የመንፈስ ጥንካሬ፣ ያልተገባ እስር (12 ዓመት) ከምኞት ወጥቶ ተራ ሰው መሆን፣ በስተእርጅና ጤና ማጣት ሳይበግራቸው ሁሌም ማንበብ፣ መማርና እስከ መጨረሻው ቀናት ለሀገር መስጠትን ተምረናል።››

**ሻሎም ! አሜን ።**

# የወጣትነት ውጣ ውረድ በበረሀ

ስምስም መንግሥቱ

ሰዎች መልካም ነገር ሲደረግላቸው አፀፋቸው ምስጋና እና ምርቃት ይሆናል:: በተለይም አዛውንቶች ሲመርቁ በሰዎች ልብ ውስጥ ያለውን ወይም የሚያስቡት ነገር የተፈፀመ ያህል ስሜት አለው:: ጥሩ ስሜት ከሚፈጥሩ ምርቃቶች መካከልም ‹‹የጠዋት ጀንበር አትጥለቅብህ (ሽ)›› የሚለው ትርጉም ይሰጣል:: ወንድም ሆነ ሴት፤ ወጣትነታቸውን በዋዛ ፈዛዛ ከማሳለፍ ለቁምነገር ቢያውሉት በማምሻው እድሜያቸው ትርፋማ ያደርጋቸዋል እንደማለት ነው::

ይህም ቢሆን ግን ሁሉም የወጣትነት ሩጫ የሀብት ማማ ላይ ያስቀምጣል ተብሎ ግን አይጠበቅም:: ልፋትና ድካሙ በሚፈለገው ያህል ፍሬ ላያፈራ ይችላል:: ነገር ግን ‹‹ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም››ና ብለፋም ብደክምም አይሳካም ብሎ አፍላ የወጣትነት ጊዜን በከንቱ እንዲያልፍ ማድረግ የዋህነት ነው:: ጉዳቱም መልሶ ለራስ ነው የሚሆነው::

የዛሬ እንግዳችን ወይዘሪት አበራሽ ማሞ የህይወት መርሀቸው ይህንኑ በመግቢያዬ ላይ ካነሳሁት ሃሳብ ጋር የተያያዘ ነው:: ወይዘሪት አበራሽ፤ ከታዳጊነት እድሜዬ ጀምሮ በኑሮ ተፈትኛለሁ ይላሉ:: ምን ገጠማቸው፤ እንዴትስ ተወጡት፤ አሁንስ በምን ሁኔታ ላይ ናቸው? የሚለውን ከመጀመሪያው ጀምሮ እንዲህ አጫወቱናል ::

የአንድ በግ ዋጋም ሦስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም ነበር ቆዳ መልስ የሚገዛው:: ቆዳውን በነፃ ስለሚወስድ ያረደበትን ዋጋ አይጠይቅም


ፎቶ- ሀዲስ አብርሃ

### አስተዳደጋቸው

ወይዘሪት አበራሽ ማሞ፤ የተወለዱት አዲስ አበባ ከተማ ቄራ ተብሎ በሚጠራ ሰፈር ነው:: በእናትና አባት የማደግ እድል አላገኙም:: ለዚህ ምክንያቱ ወላጅ እናታቸው እርሳቸውን ለማሳደግ የገንዘብ አቅም ስላልነበራቸውና አስቸጋሪ በሆነ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ በመሆናቸው ነው:: በአጋጣሚ ክርስትና ያነሷቸው ወይዘሮ ሙሉነሽ ካሳ ከአካባቢው ላይ ጥሩ ኑሮን የሚኖሩትና ሀብታም ተብለው ከሚጠሩት ግለሰቦች መካከል አንዷ የነበሩ በመሆኑ እናታቸው እርሳቸው እንዲያሳድጓቸው ሰጧቸው::

በክርስትና እናታቸው ቤት ብዙ የቤት ሰራተኞች ነበሩ:: በወቅቱም ሰራተኞች ባሪያ እንደሚባሉም በክርስትና እናታቸው ቤት ሲያድጉ ነው ያወቁት:: እነዚህ በአሰሪዎቻቸው ባሪያ የሚባሉትም ግደበረት ከሚባል አካባቢ ተገዝተው እንደሚመጡም ያውቃሉ:: እርሳቸውም በማደጎ ቢወሰዱም እንደ ልጅ አልነበርም የሚታዩት:: ከቤት ሰራተኞቹ ባልተናነሰ በቤት ውስጥ የታዘዙትን ሥራ ሁሉ መስራት ይጠበቅባቸዋል:: ቤት አጽድተው፣ ለክርስትና እናታቸው ባለቤት ቡና አፍልተው ካጠጡ በኋላ ነው ወደትምህርት ቤት የሚሄዱት::

የትምህርት ሰአት ስለሚደርስባቸው ቁርስ እንኳን ለመብላት ጊዜ የላቸውም:: መደበኛ ቁርስ አያውቁም:: የክርስትና እናታቸው ባል በሚያጎርሷቸው ጉርሻ ነው ትምህርት ቤት ውለው የሚመለሱት:: ትምህርት ቤትም በጊዜ ስለማይደርሱ የአስተማሪ ቅጣት ይደርስባቸዋል:: አንዳንዱ መምህር አሸዋ ላይ በማንበርከክ ነው የሚቀጣው:: ቅጣቱ ተደጋጋሚ ስለሆነባቸው ጉልበታቸው ላይ ጉዳት ደርሶባቸዋል:: አንድ መምህርም ሲገርፏቸው በመግረፊያው አይናቸው ላይ ጉዳት አስከትሎባቸው ለብዙ ጊዜ ታመው ያውቃሉ ::

በወቅቱ በተደጋጋሚ የሚያረፍዱበትን ምክንያት የጠየቃቸውም፣ የሚረዳቸውም አስተማሪ አለመኖሩም ያሳዝናቸዋል:: እርሳቸውም እውነታውን ለመናገር ይፈሩ ስለነበር ቅጣቱን ከመቀበል ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም:: ትምህርታቸውን ላለማቋረጥ እንዲህ ያለውን ፈተና ለመቀበል ተገደው እንደነበር ነው ለትምህርት የከፈሉትን ዋጋ የሚናገሩት::

እንደ ልጅ ይሄን እፈልጋለሁ ያሉበትን ጊዜ አያስታውሱም:: ልብስም የሚገዛላቸው በአሳዳጊያቸው ፍላጎትና ምርጫ ነው:: ይጠሩ የነበረውም በወላጅ አባታቸው ሳይሆን በክርስትና እናታቸው ባል ነው:: በዚህ ሁኔታ ተምረውም አምስተኛ ክፍል ደርሰዋል::

ወላጅ እናታቸው እርሳቸው የሚያድጉበት ቤት ይመጡ ነበር:: አመጣጣቸው ልጃቸውን ለማየት ሳይሆን የክርስትና እናታቸው ‹‹ለምን ቤቴን አልፊሽ ትሄጃለሽ እየመጣሽ ምሳ ለምን አትበይም›› የሚል ወቀሳ ስላቀረቡላቸው ነበር:: እናታቸውም ወቀሳውን ተቀብለው በተባሉት ሰአት ምሳ ለመብላት ልጃቸው ወዳሉበት ቤት ይመላለሱ ነበር::

ግን የሚደረግላቸው መስተንግዶ የወቀሳውን ያህል አለመሆኑን ወይዘሪት አበራሽ ይታዘባሉ:: ይናደዳሉ:: ወይዘሪት አበራሽ እንደሚሉት የሚቀርበው ምግብ ከሽሮ ያለፈ አይደለም:: ያም ቢሆን ደጅ ጠንተው ነበር የሚቀርብላቸው:: እንኳን እናታቸው እርሳቸውን ጨምሮ የቤት ሰራተኞች ለባለቤቶቹ ከሚዘጋጀው ምግብ መብላት አይፈቀድላቸውም:: ለሰራተኞች ተብሎ ሌላ ምግብ ይዘጋጃል::

ተመርጦ የሚቀርበውንም ምግብ እናታቸው በሰአቱ አለማግኘታቸው ከንዴት አልፎ አስለቅሷቸው ያውቃል:: እናታቸው እንዳያዩዋቸው ጓሮ ሄደው ነበር አልቅሰው ንዴታቸውን ተቆጣጥረው የሚመለሱት:: እናታቸውም ምግብ መጠበቁ ሰልችቷቸው አንድ ቀን ሳይበሉ ከቤቱ ወጥተው ይሄዳሉ:: ወይዘሮ አበራሽን ይበልጥ ያናደዳቸው ደግሞ የክርስትና እናታቸው ንግግር ነበር:: የባለቤታቸውን ስም ጠርተው ከእርሱ በፊት ምግብ እንዲቀርብላት ፈልጋ ነበር እንዴ? ያሉትን አይረሱትም:: ወይዘሮ አበራሽ እንደሚሉት፤ እናታቸው የክርስትና እናታቸው ባል ተመግበው እስኪጨርሱ ጠብቀው ምግብ መብላታቸው ትርጉም አልነበረውም:: ምክንያቱም ለእናታቸውና ለክርስትና እናታቸው ባል የሚቀርበው ምግብ የተለያየ በመሆኑ::

ወይዘሪት አበራሽ እንደሚሉት፤ ወደፊት ጥሩ የሆነ ህይወት ይገጥመኛል የሚለውን በማሰብ ይሄም ያልፋል ብለው ነገሮችን ለመቋቋም ብዙ ጥረት አደረጉ:: ችግሮችን ተቋቁመው ትምህርታቸውን ለመጨረስና የተሻለ ደረጃ ላይ ለመድረስ ፈለጉ ነገር ግን ከእርሳቸው አልፎ እናታቸው የሰው ፊት የማየታቸው ሁኔታ እስከመቼ የሚለው አእምሮአቸውን እረፍት ነሳው፤ የተገኘውን ሥራ ሰርተው እናታቸውን በኑሮ ማገዝ እንዳለባቸው ተሰማቸው፤ ይህ ሃሳባቸውም አሸንፎ ወይዘሪት አበራሽ ከክርስትና እናታቸው ቤት ወጡ ::

### የአንድ ቀን ውሳኔ

ወይዘሪት አበራሽ ካሳደጓቸው ከክርስትና እናታቸው ቤት ለመውጣት ሲወስኑ፤ ተደብቀው ደብተሮቻቸውንና ልብሳቸውን በአጥር ወደ እናታቸው ቤት በመወርወር ነበር፤ የእናታቸውን የቤት ቁልፍ ከጎረቤት ወስደውም ነው ወደ ቤት የገቡት:: እናታቸው ለምን ይሄን አደረግሽ ብለው እንደሚቆጧቸው ስለሚያውቁም ቤት ገብተው አልጋ ስር ነበር የተደበቁት:: እናታቸው ቤት ገብተው ስላላገኟቸው ሁኔታውን ለመጠየቅ ልጃቸውን ወዳሳደጓት ሴት ቤት ሄዱ::

እርሳቸው ገና ለመጠየቅ ሲሉ ሴትየዋ ቀድመው ‹‹ምን ልታደርጊ መጣሽ ልጅሽን እንደሆን ወስደሻል›› አሏቸው:: ያልጠበቁት ነገር ስለነበር ደንግጠው ‹‹ልጄ ጠፋች ማለት ነው›› ብለው ወደቤታቸው ተመልሰው ቁልፍ የሰጡትን ጎረቤት ይጠይቃሉ:: ይህ ሁሉ ሲሆን ወይዘሪት አበራሽ አልጋ ስር እንደተደበቁ ናቸው:: በመጨረሻ እናታቸው እንዳይመቷቸው ተማጽነው ከተደበቁበት ይወጣሉ::

እናታቸው በዚህ ሁኔታ ካሳደጓቸው ሴት ቤት መውጣት እንዳልነበረባቸው በቁጣም በምክርም ጭምር ሊያግባቧቸው ሞከሩ:: እናታቸው ጎረቤት ስለሆኑ ሲወጡና ሲገቡ ሊደርስባቸው የሚችለውን አላስፈላጊ የሆነ ንግግር በማሰብ ጭምር ነበር ልጃቸው ያደረገችውን ነገር ትክክል እንዳልሆነ ለመገሰጽ የሞከሩት:: ወይዘሪት አበራሽ ግን አንዴ ስለቆረጡ እናታቸው የማይቀበሏቸው ከሆነ “አባሳሙኤል” የሚባል ወንዝ ውስጥ ገብተው እራሳቸውን እንደሚያጠፉ ይነግሯቸዋል:: እናታቸውም የልጃቸውን ማምረር በመገንዘባቸው መልሰው ያረጋጓቸዋል::

የወይዘሪት አበራሽ እራስን የመቻል ኑሮ “ሀ” ተብሎ ተጀመረ:: እርሳቸው እንደሚሉት አንድ የአካባቢያቸው ነዋሪ የሆነ ሰው ያገኙና ሥራ እንዲፈልግላቸው ይጠይቁታል:: ሰውየውም ገና ልጅ እንደሆኑና ትምህርት ቢማሩ እንደሚሻል ይመክሯቸዋል:: ደግሞም ምን አይነት ሥራ ሊሰሩ እንደሚችሉም መልሰው ይጠይቋቸዋል::

በሌላ ቀንም መልሰው ይህን ሰው ሥራ እንዲፈልጉላቸው ይጠይቃሉ:: ሰውየውም የሰሙትን ማስታወቂያ ይነግሯቸዋል:: ተቋሙ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ገነት ሆቴል አካባቢ ሲሆን፤ በዚያን ጊዜ የትራንስፖርት ዋጋም ኪስ የሚጎዳ አልነበረም:: በተለይም የከተማ አውቶቡስ ለአንድ ጉዞ 15 ሣንቲም ነበር የሚያስከፍለው:: እናታቸው ሣንቲም ከሚያስቀምጡበት ቦታ ፈልገው እስከ መመለሻቸው 30 ሣንቲም ይዘው ነበር የሄዱት::

ለእናታቸውም ሳይነግሯቸው በራሳቸው ወስነው ሥራ ፍለጋ የሄዱት:: የገና በዓል ዋዜማ ስለነበር እናታቸው ቤት “በእበት” ለቅልቀው፣ እቃ አጥበው፣ ዳቦም ደፍተው እንዲጠብቋቸው አዘዋቸው ነበር ወደ ሥራ የሄዱት:: እናታቸው ህንፃ ኮንስትራክሽን የሚባል ድርጅት ውስጥ የቀን ሥራ በመስራት በቀን 95 ሣንቲም ተከፋይም ናቸው:: የሚገኘው ገንዘብ አነስተኛ ቢሆንም የሚገዛው ነገር ርካሽ በመሆኑ በኑሮ አይቸገሩም:: በስሙኒ ስጋ ይገዛል ሚዛን ስለሌለም በሳህን ተለክቶ ነበር የሚሸጠው በማለት የወቅቱን ሁኔታ ያስታውሳሉ::

የአንድ በግ ዋጋም ሦስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም ነበር ቆዳ መልስ የሚገዛው:: ቆዳውን በነፃ ስለሚወስድ ያረደበትን ዋጋ አይጠይቅም:: ይሄ በ1970ዎቹ ውስጥ የነበረ ታሪክ ነው:: አሁን ላይ ዶሮ አርዶ በልቶ ማቅረብ የሥራ መስክ ሆኖ በአንድ ዶሮ እስከ 70 ብር የአገልግሎት ክፍያ እየተጠየቀ ነው:: አንድ በግ አርዶ ለመበለት ደግሞ እስከ አምስት መቶ ብር ደርሷል:: ይሄ ሁሉ ለውጥ ብዙ ረጅም ጊዜ የሚባል አይደለም:: የጤፍ ዋጋም ቢሆን አሁን ካለው ጋር በንጽጽር እንኳን የሚቀርብ አይደለም በማለት ትዝብታቸውን ያነሳሉ::

አንድ ኩንታል ጤፍ ከ50 ብር የበለጠ አይደለም:: እንደ ምስር፣ባቄላ ያሉ ጥራጥሬዎች በሳንቲም ነው የሚሸጡት:: ወተትም ቢሆን አቅርቦትም ሆነ ገበያውም ቅሬታ የሚቀርብበት አልነበረም :: ሰዎች እነዚህን ሁሉ ፍላጎቶቻቸውን የሚያሟሉት በሚያገኙት አነስተኛ ገቢ ነው::

እውነት የማይመስል ግን ደግሞ እውነት የሆነን ነገር ኖሮ ካየው ሰው መስማት ደስ ይላል:: ‹‹ማን ይናገር የነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ›› ይባል የለ ከነአባባሉ:: ኑሮ ድሮና ዘንድሮ ሆኖብን ንጽጽር ውስጥ ጭልጥ ብለን ገባን:: ወደ ወይዘሪት አበራሽ የሥራ ቅጥር ተመልሰናል:: እርሳቸው እንዳሉት ሥራ መቀጠሩ ግድ ነበር:: እናታቸው የቀን ሥራ ከሚሰሩበት ድርጅት ተቀንሰው ቤት ውለዋል:: ምንም እንኳን ኑሮ ርካሽ ቢሆንም ገቢ ከሌለ ችግር ውስጥ መግባት አይቀርምና አሁን እሳቸውም በሙሉ አቅማቸው ተንቀሳቅሰው ሥራ ማግኘት የመኖር ጉዳይ ሆኖባቸዋል:: እስከ እዛ ድረስ እንኳን ከእናታቸው ጋር ለመኖር ያላቸው ገቢ ወላጅ አባታቸው ደብረዘይት አየር ኃይል ተብሎ የሚጠራ

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## የወጣትነት ውጣ ውረድ...

ከ7ኛ ገጽ የዞረ

ተቋም ውስጥ ይሰሩ ስለነበር በወር 50 ብር ተቆራጭ የሚልኩላቸው ነው::

ወይዘሪት አበራሽ ሥራ ፍለጋ የሄዱበት መሥሪያ ቤት ሰራተኞች ለሰሩበት ሥራ የቀን ውሎ አበል ክፍያ እየፈፀሙ ነበር የደረሱት:: ወይዘሪት አበራሽም ሥም ሲጠሩ የነበሩትን ሰው ጠጋ ብለው ሥራ እንደሚፈልጉ ጠየቋቸው:: ሰውየውም ልጅ መሆናቸውን አይተው ሊቀበሏቸው ፍቃደኛ አልነበሩም:: ሆኖም ግን የያዙትን የሥም ዝርዝር በመጥራት እንዲያግዟቸው ይጠይቋቸዋል::

እርሳቸውም ፈቃደኛ ይሆናሉ:: ሥም ጥሪው እንዳለቀ ሰውየው የመልእክት ሰራተኛ ትሆናለች ብለው በማሰብ በቀሩ ሰዎች ምትክ ወይዘሪት አበራሽን መዘገቧቸው:: አሁን ወይዘሪት አበራሽ ይጠሩባቸው የነበረው የአሳዳጊያቸውን ስም በወላጅ አባታቸው በአቶ ደስታ ገብረሥላሴ ለመቀየር መልካም አጋጣሚ ተፈጠረላቸው::

ወይዘሪት አበራሽ ሲቀጠሩ የ13 አመት ታዳጊ ነበሩ:: የቀጠራቸው መከላከያ ኮንስትራክሽን ድርጅት በኦሮሚያ ክልል በነቀምት መካከል ላይ በምትገኘው አርጆ ደዴሳ ላይ ማሰልጠኛ ጣቢያ ለማሰራት ዝግጅት ላይ ስለነበር ቅጥሩም የተፈፀመው ለዚህ ተቋም ነው:: የደመወዝ ስምምነቱ ለእርሳቸው ግልጽ ባይሆንም ቅጥሩ ኮንትራት እንደሆነና በወር 90 ብር እንደሚከፈላቸው ያውቃሉ:: በማግስቱ ጉዞ ወደ ደዴሳ በመሆኑ ከሰአት በኋላ አበል እንዲወስዱ ተነገራቸው:: ከሚያገኙት ብር ላይ ለእናታቸው 50 ብር እንዲሰጣቸው አስቀድመው ውል በመግባታቸው:: ተቋሙ ውላቸውን ተቀበላቸው:: ቅጥሩ እንደተፈፀመም በቀን የታሰበላቸው የውሎ አበል ስድስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም ነበር:: ወይዘሪት አበራሽ ለጉዞ የሚሆን ዳቦቆሎ ስንቅ ለመያዝ በእጃቸው ላይ በነበረው 10 ብር በአንድ ብር ከአምስት ሳንቲም አንድ ኪሎ ስኳር፣ በሁለት ብር ከሃምሳ ሣንቲም ዱቄት፣ በሁለት ብር ግማሽ ሊትር ዘይት፣ ገዝተው ነበር ወደ ቤታቸው የተመለሱት::

ወደ አርጆ ደዴሳ ለመሄድ መዘጋጀታቸውን እናታቸው እንዳያውቁ ዳቦቆሎው ጎረቤት እንዲዘጋጅ ነበር ያደረጉት:: ጎረቤታቸው በምስጢር እንዲይዙ ተማፀኗቸው:: በወቅቱ አስቸጋሪ የሆነባቸው ለጉዞ ሲነሱ ለእናታቸው ምን ብለው እንደሚነግሯቸው ነበር:: እትዬ የሺ የሚሏቸው ጎረቤታቸው ዘዴ እንደማያጡና ጉዞአቸውን እንደሚያሳኩላቸው ነገሯቸው::

በቆየው ባህል አንድን ሰው ለማሳመን ወይንም የሚጠይቋቸው ነገር ተቀባይነት እንዲያገኝ ድንጋይ ተሸክመው ወይንም ነጠላቸውን አንጥፈው ነው ልመናቸውን የሚያቀርቡት:: እትዬ የሺም ድንጋይ ተሸክመው ነበር ለወይዘሪት አበራሽ እናት ጥያቄያቸውን እንዲቀበሏቸው የተማፀኗቸው:: በቅድሚያ እሺ ካስባሏቸው በኋላ ወይዘሪት አበራሽ ሥራ አግኝተው ወደ ደዴሳ ማሰልጠኛ እንደሚሄዱ ሲነግሯቸው ግን በጣም ነበር የጮሁት:: « አንዲት ልጅ ብትኖረኝ ልጄን ሸጠው ጠበቁኝ» እያሉ ነበር እያለቀሱ ሲጮኹ የነበረው:: መረጋጋት አቃታቸው:: በሁኔታቸው የተደናገጡት እትዬ የሺ ያሳምናቸዋል ያሉትን ሁሉ ሃሳብ በማቅረብ እንዲረጋጉ ጠየቋቸው:: እንዲያምኗቸውም ሌሎች ለመሄድ የተዘጋጁ የአካባቢው ልጆች መኖራቸውንም ነገሯቸው:: የወይዘሪት አበራሽ እናት «አፈሳ ካልሆነ በስተቀር እንዴት የአንድ አካባቢ ልጆች ሊሄዱ ይችላሉ» በማለት ነገሩን አምኖ ለመቀበል ከበዳቸው:: እትዬ የሺ ከብዙ ድካም በኋላ አሳምነዋቸው እንዲቀበሉ አደረጓቸው:: ከተረጋጉ በኋላም ያስፈልጋቸዋል ያሉትን ሁሉ አዘጋጅተው ልጃቸውን መርቀው ሸኟቸው::

### የመጀመሪያው የሥራ ቅጥር በአርጆ ደዴሣ

ወደአርጆ ደዴሣ የጉዞ መነሻው ከአዲስ አበባ ከተማ ገነት ሆቴል ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ነበር:: ተጓዦች በሰአታቸው ነገኙተዋል:: ወይዘሪት አበራሽ እንደነገሩኝ፤ ከተጓዦች መካከል በእድሜ ትንሿ እርሳቸው ነበሩ:: የተቀሩት እናታቸው የሚሆኑ ሴቶች ናቸው:: ለምን ሥራ እንደተቀጠሩ ሲጠይቋቸውም ቡኮ ቤት፣ እንጀራ ቤት፣ ወጥቤት፣ ረዳት ብለው ስለሚሰሩት ሥራ ነገሯቸው:: ተላላኪ የሚል የሥራ መድብ ያላቸው እርሳቸው ብቻ እንደሆኑ አረጋገጡ::

**ሀብቱን በማስመለሳቸው ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ደራርቱ ቱሉና ሌሎችም አትሌቶች በሩጫ ያገኙት ድል ያህል እንደተሰማቸው ይናገራሉ:: አካባቢው ላይ የወርቅና የነዳጅ ማዕድን ሀብት መኖሩንም እግረ መንገዳቸውን ነገሩኝ:: ኢትዮጵያ ያልተነካ ሀብት እንዳላት አጫወቱኝ**



እናታቸው ሲሸኟቸው አደራ የሰጧቸው ለነዚህ ሴቶች በመሆኑ፤ የአደራ ልጄ የሚለው ስያሜ በጉዞ ላይ እያሉ ነበር የተጀመረው:: ሥራቸው ቦታ ሲደርሱ ቆርቆሮ በቆርቆሮ በተሰራ ማደሪያ ቤት ((ካምፕ) ውስጥ ነበር የገቡት:: መኝታውም ምግቡም ከድርጅቱ በመሆኑ ለግላቸው የሚያስፈልጋቸውን ማሟላት ካልሆነ በቀር ወጪ የለባቸውም:: ሥራውንም አካባቢውንም በጊዜ ሂደት ለመዱት:: ሥራውንም እየወደዱት መጡ:: በተለይ ደግሞ ለእናታቸው ቡና፣ ከሰል፣ ማር፣ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እየገዙ መላክ መቻላቸው በጣም ነበር ያስደሰታቸው:: ካለእድሜያቸው ትምህርታቸውን ትተው ሥራ ለመቀጠር የፈለጉት እናታቸውን ከችግር ለማውጣት በመሆኑ የሚችሉትን ሁሉ ያደርጉ ነበር ::

ወይዘሪት አበራሽ የሰውነት ለውጥ ማምጣታቸው፣ በተቋሙም ውስጥ በእድሜ ልጅ መሆናቸው እይታ ውስጥ እንዲገቡ አደረጋቸው:: ልጅነታቸውን ለመጠቀም ጥረት የሚያደርጉ ወንዶችም እየበዙ መምጣታቸው ግራ እንዲገባቸው እንዳደረጋቸው ያስታውሳሉ:: እርሳቸው እንደሚሉት በቀላሉ እንዳይታለሉም ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር:: አንድ ቀን ግን ማለፍ የማይችሉት ሁኔታ ተፈጠረ:: የአንዲት ሰራተኛ ሸኝት መርሀ ግብር ተዘጋጅቶ ነው ነገሩ የሆነው::

ያልፈቀዱት ሰው ባላሰቡት ሁኔታ አስገድዶ መድፈር ፈፀመባቸው:: እርግዝናም ተከሰተ የሆነው ነገር ከእርሳቸው ዓላማ ጋር የሚሄድ ሆኖ ስላላገኙት እና ድርጊቱንም የፈፀመውን ሰው ማነጋገር ስላልፈለጉ የወሰኑት ከአካባቢው መራቅን ብቻ ነው:: ሥራቸውን ትተው ወደ አዲስ አበባ ከተማ በመመለስ ጽንሱን እንደማይፈልጉት ለሀኪም አማክረው ውርጃ አካሄዱ:: እናታቸው እንዳያዝኑባቸው በወቅቱ በሚስጢር ነበር ያደረጉት::

### ከአርጆ ደዴሳ ወደ ጋምቤላ እና አፋር ሥራ የቀየሩበት አጋጣሚ

ወይዘሪት አበራሽ፤ በአርጆ ደዴሣ በነበራቸው የአራት ዓመት የሥራ ቆይታ የተለያዩ ነገሮችን ለማወቅ ችለዋል:: በእድሜም ከፍ ማለታቸው ለነገሮች ሁሉ ትኩረት እንዲሰጡ አድርጓቸዋል:: እንደ አዲስ ሥራ ለመቀጠር ህንፃ ኮንስትራክስን ተመልሰው ሄዱ፤ ድርጅቱ ጋምቤላ ላይ የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ሲያካሂድ ለባለሙያዎች ምግብ የሚያዘጋጁና የተለያዩ የቢሮ ሥራ የሚሰሩ ሰራተኞች ያስፈልጉት ስለነበር ነው ቅጥር የፈፀመው:: ወይዘሪት አበራሽም ወደ ጋምቤላ ሲሄዱ ረዳት የወጥቤት ሰራተኛ ሆነው ነበር:: በክርስትና እናታቸው ቤት ሲያድጉ ምግብ የሚያበስሉ የቤት ሰራተኞች ጋር ይውሉ ስለነበር በማየት ብዙ ነገሮችን በልጅነት አእምሮአቸው መያዝ ችለዋል:: ይህ ሁሉ ተሞክሮ ነው በቀላሉ የወጥቤት ሥራውን ለመሥራት ያስቻላቸው::

በጋምቤላ ረዳት የወጥ ቤት ሰራተኛ ሆነው የሰሩት ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነበር:: አቅማቸው ታይቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ዋና ወጥ ቤትነት ተዘዋወሩ:: ከፈረንሳይ፣ ከአሜሪካና ከተለያዩ ሀገራት ለሚመጡ እንግዶች የሚሆን ምግብ እንዲያዘጋጁ ሲታዘዙም የውጭዎቹ የሚመርጧቸው እንደ ፓስታፉሩኖ የመሳሰሉ ምግቦችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ:: «በችሎታዬ ወጥቤቱን ተቆጣጠርኩት:: በሥሬም ሰራተኞች ስለነበሩ አሰራለሁ» በማለት ነበር ችሎታቸውን የገለጹት::

በጋምቤላ በነበራቸው የሥራ ቆይታ ደስተኛ ነበሩ:: በእረፍት ጊዜያቸውም የሚሰራውን የአውሮፕላን ማረፊያ ሄደው በመነበኘት ማስታወሻ ፎቶግራፍም ይነሱ እንደነበር ነው የሚናገሩት:: ጋምቤላ በነበራቸው ቆይታ የሚያስታውሱት ከገጠር ማር፣ ፍራፍሬ ይዘው የሚመጡ ሰዎች ድካም ነበር:: ብዙ ይዘው መጥተው በርካሽ ነው የሚሸጡት:: ስለሚያሳዝኗቸውም ምግብ ይሰጧቸው ነበር::

በቋንቋ ባይግባቡም በሃሳብ ስለሚግባቡ ጥሩ ግንኙነት ፈጥረው ነበር:: አንዳንዶችም ማር በስጦታ ያበረክቱላቸው እንደነበር በማስታወስ የሰው ልጅ ለመቀራረብ፣ ለመዋደድ ቋንቋ፣ ዘር እንደማይገድበው ይህንን እንደ ማሳያ ያቀርባሉ:: ነቀምት ከተማ ለጋምቤላ ቅርብ በመሆኑ ለቤተሰብ ስልክ ለመደወል፣ የባንክ አገልግሎት ለማግኘት፣ለገበያና ለመዝናናት ይሄዱ እንደነበርም ያስታውሳሉ::

አንድ ጊዜ በወባ ትንኝ ተነድፈው ታመው በአንቶኖቭ አውሮፕላን ወደ ቢሾፍቱ (ደብረዘይት) ተልከው ህክምና ተደርጎላቸው ወደ ሥራ የተመለሱበትን ጊዜ ብቻ ነው በነበራቸው የሥራ ቆይታ የሚያስታውሱት:: የጋምቤላ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ሥራ ሲጠናቀቅ ነው የኮንትራት ሥራው ያበቃው::

ወደ አዲስ አበባ ከተማ ለመመለስ ዝግጅት ላይ እያሉ፤ እህል ውሃቸው ከጋምቤላ እንዲለቁ አላደረጋቸውም ድርጅታቸው እዛው ባሮአኮቦ ፕሮጀክት ስለነበረው የሚፈልገውን ሰራተኛ ሲመርጥ አንዷ ወይዘሪት አበራሽ ሆኑ:: ወይዘሪት አበራሽ ስለፕሮጀክት ሥራዎችም ጠንቅቀው ስለሚያውቁና ባለሙያዎችም እንደሚቀርቧቸው፣ ስለሥራቸውም ለማወቅ ጥረት ያደርጉ እንደነበርና ቀረቤታ መፍጠራቸውም እንደነርሱ የተማሩ ያህል እንዲሰማቸው እንዳደረጋቸውም ያስታውሳሉ:: የባሮአኮቦ ፕሮጀክት ለመስኖ አገልግሎት የሚውል አቦቦ ላይ ግድብ ነበር የሚሰራው::

አንድ ቀን፤ ከአቦቦ ወደ ጋምቤላ ከተማ በመኪና በመጓዝ ላይ እያሉ፤ የመገልበጥ አደጋ ያጋጥማቸዋል በአጋጣሚ ጀሮአቸው አካባቢ ከደረሰባቸው መጠነኛ ጉዳት በስተቀር የከፋ ችግር አልነበረም:: እርሳቸው እንዳሉት፤ ይህ ገጠመኝ ቀድሞ ከጋምቤላ ሌላ ቦታ ለመሄድ የነበራቸውን እቅድ አፋጠነው:: አፋር ክልል ዱብቲ መሥራት ነበር ፍላጎታቸው:: የፕሮጀክቱ ሥራ ከባሮ ፕሮጀክት ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ቦታ ለመቀየር ቀላል ነበር የሆነላቸው:: ሥራቸው አሁንም ወጥቤት ነው:: የዱብቲው ፕሮጀክት ሥራ ደግሞ ተንዳሆ እርሻ ልማት ሥራ ነው:: የፕሮጀክት ሥራዎቹን የሚያሰራው በወቅቱ የውሃ ሀብት ልማት የሚባል ተቋም ነው::

### የሥራ አካባቢ በረሀ መሆን፤

ወይዘሪት አበራሽ ረጅሙን እድሜያቸውን በሥራ ያሳለፉት በረሀ አካባቢ ነው:: ፈታኝ የሆኑ ነገሮችን ማሳለፋቸውን ነው የሚናገሩት :: እባብን ጨምሮ በስም የማያውቋቸው የተለያዩ ነፍሳት በመኖራቸው በነዚህ የመነከስና ለጉዳት የመጋለጥ እድሉ ሰፊ ነው:: ሙቀቱም ኃይለኛ ነው:: በተለይም በቤት ውስጥ የሙቀት መከላከያ ማድረግ ካልተቻለ ከባድ ነው:: አንዳንዴ ሙቀቱ በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚጨምር ለጤና ችግር ይዳርጋል:: ውሃው እንኳን ለመጠጥ ለማዋል ለሰውነት መታጠቢያ ይፋጃል:: ምግብም አንዴ የተዘጋጀው ላንድ ጊዜ ነው መዋል ያለበት እንጂ ይበላሻል::

### የማዕድን ሀብት ያዳኑበትና የተከሰከሰ አውሮፕላን ስባሪ ያገኙበት አጋጣሚ

አፋር ዱብቲ ውስጥ ሲሰሩ ነው በፕሮጀክቱ ውስጥ ከሚሰሩት አንዱ የሆነው የሩሲያ ዜጋ የሬሣ ሳጥን አስመስሎ በሰራው ሳጥን ውስጥ የወርቅ ማእድን ያከማቻል:: ወይዘሪት አበራሽ ስላልጠረጠሩ በሩሲያ ቋንቋ ምን እየሰራ እንደሆነ ጠይቀውት በዋዛ ነበር ያለፉት:: ነገሩ እንቅልፍ ነሳቸው:: ስለከነከናቸው ተመልሰው ሲያረጋግጡ የወርቅ ማዕድን ነው ሳጥኑ ውስጥ የከተተው::

ሰውየው ጭኖ ለመሄድ አዘጋጅቷል:: ቴሌ ሄደው በስልክ ለቦሌ አየር ማረፊያ መረጃ በመስጠት ሀብቱ እንዲድን ያደረጉበትን አጋጣሚ አይረሱም:: ሀብቱን በማስመለሳቸው ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ደራርቱ ቱሉና ሌሎችም አትሌቶች በሩጫ ያገኙት ድል ያህል እንደተሰማቸው ይናገራሉ:: አካባቢው ላይ የወርቅና የነዳጅ ማዕድን ሀብት መኖሩንም እግረ መንገዳቸውን ነገሩኝ:: ኢትዮጵያ ያልተነካ ሀብት እንዳላት አጫወቱኝ::

በጋምቤላ ሲሰሩ ደግሞ በአደጋ አውሮፕላን ተከስክሶ ገደል ውስጥ ይገባል:: ያወቀ ሰው አልነበረም:: እርሳቸውና አንድ ሰው ሆነው ሲፈልጉ እርሳቸው ነበሩ ስባሪውን ቀድመው ያገኙት:: መረጃውን ከሰጡ በኋላ ግን በውስጡ ጀኔራሎች እንደነበሩና አስከሬናቸውም እንዳልተገኘ በባለሙያዎች ተረጋገጠ:: አደጋውም በአሞራ የደረሰ መሆኑ ነው የተገለጸው ይላሉ:: ስባሪው በተራ ሰው የተገኘ መሆኑ ሲነገር ወይዘሪት አበራሽ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቷቸው እንደነበር ያስታውሳሉ::

### ከበረሀ የተመለሱበት አጋጣሚና አሁን የሚሰሩበት መሥሪያ ቤት

ወይዘሪት አበራሽ የመንግሥት ለውጥ ሲደረግ ነው ይሰሩ ከነበሩበት አፋር ዱብቲ የወጡት:: በወቅቱ ከፍተኛ መደናገጥ መረበሽም ስለነበር መውጣታቸውን እንጂ ምን መያዝ እንዳለባቸው እንኳን አያውቁም ነበር:: ወይዘሪት አበራሽ አሁን በቆላማና መስኖ ሚኒስቴር ውስጥ የመልእክት ሰራተኛ ሆነው ነው የሚያገለግሉት::

### የቤተሰብ ሁኔታ

ወይዘሪት አበራሽ፤ ያለፈቃዳቸው፣ ስለማንነቱም በቅጡ የማያውቁት ሰው አስገድዶ ስለደፈራቸው:: የሥነልቦና ጫና እንዳሳደረባቸው ይናገራሉ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለወንድ ጥሩ የሆነ አመለካከት የላቸውም:: እንዲቀርባቸውም አይፈልጉም:: በኃይለ ቃል ነው የሚያነጋግሩት:: «አውሬ ሆንኩ» ሲሉም ለወንዶች ያደረባቸውን ጥላቻ ይገልጻሉ:: ድርጊቱ ከተፈፀመ ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ እንኳን ለመርሳት አልቻሉም:: ይህ ደግሞ ትዳር ለመያዝ ተጽእኖ አሳድሮባቸዋል:: በዚህ የተነሳም ትዳር አልመሰረቱም:: ከትዳር ውጪ የወለዷቸው ሁለት ልጆች አሏቸው::

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

## የምሥራቁ ክፍል የማይዳሰስ ቅርስ- የቱሪዝም ዘርፉ ተስፋ

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ የበርካታ ባህሎችና ሃይማኖቶች መገኛ ነች። በዓለማችን ላይ በህብረ ብሄራዊነትና በብዝሀ ሃይማኖት ከሚታወቁ ሀገራት ቀዳሚውን ስፍራም ትይዛለች።

ሀገሪቱ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ ሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በርከት ያሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ /የማይዳሰሱ/ ቅርሶችን ማስመዝገብም ችላለች። ከእነዚህ ውስጥ መስከረም 17 የሚከበረው መስቀል፣ በዚሁ ወር የሚከበረው የኢሬቻ በዓል እንዲሁም ከጥር 10 እስከ 12 የሚከበረው ጥምቀት እንዲሁም የፍቼ ጨምበላላ በዓላት ይገኙበታል።

ከዚህ በተጨማሪ በምሥራቁ ክፍል በምትገኘው የሀረሪ ክልል ብሄረሰብ በልዩ ድምቀት የሚከናወን ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓትን አጣምሮ የያዘውን የሸዋልኢድ በዓል ስነ ሥርዓት ለዓለም ሕዝብ አበርክታለች። ዩኔስኮም ይህንን ደማቅ ሥነ ሥርዓት በቅርቡ በዓለም ቅርስነት በይፋ መዝግቦታል።

ሸዋልኢድ በድምቀት የሚከበረው በአንጋፋዋና ጥንታዊቷ የሀረር ከተማ ነው። በዓሉ በሀረሪ ሕዝብ ባህላዊ በዓል ሆኖ እንዲከበር በአዋጅ የተደነገገው ጥቅምት 8 ቀን 1999 ዓ.ም ሲሆን፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮና በኋላም ባህላዊ እሴቱ እየጎላና እየበረታ ሄዶ፣ ከሀረር አልፎ የኢትዮጵያ፣ ከኢትዮጵያ ተሻግሮም የዓለም ቅርስ ለመሆን በቅቷል።

የበዓል አከባበሩን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ በ2012 የተጀመረው ሥራና ጥረት ውጤት አምጥቶ የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የበዓሉን አከባበር ከዓለም የማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል መዝግቦታል።

የአንድ ማህበረሰብ ባህልና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ለባለቤቱ ከሚሰጡት ጥልቅ ትርጉም ባሻገር ሰፊ አንድምታ የያዙ መሆናቸው ይገለፃል። በተለይ የማህበረሰብ ባህላዊ ልምምዶች የእርስ በእርስ መስተጋብርንና እሴቶችን ያጎለብታሉ፤ በተጨማሪም የቱሪዝም ዘርፍ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ መሆኑን በዘርፉ ሰፊ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይናገራሉ። በተለይ የአንድን ሀገር ቱሪዝም ለማሳደግ ከማይዳሰስ ቅርስ ውስጥ የሚመዘገቡ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓቶች ግዙፍ ድርሻ አላቸው።

ሸዋልኢድም ይህን መሰል እምቅ አቅም ካላቸው የዓለማችን የማይዳሰሱ ቅርሶች ተርታ የተመደበ ነው። በየዓመቱ በጥንታዊቷ ሀረር ከተማ የሚከበረው ይህ ተወዳጅ ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓል ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ላይ ይበልጥ ጎልታ እንድትታይ ከማድረግ ባሻገር ሰፊ የቱሪስት ፍሰት እንዲኖር የማስቻል አቅም እንዳለው ይገለፃል። የዘንድሮው ዓመታዊ በዓልም ባሳለፍነው ሳምንት በከተማዋ ሲከበር ይህንን የማይተካ ሚናውን ለማጉላት እንደሚሰራ ተገልጿል።

‹‹ኢትዮጵያ የአስደናቂ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ፀጋዎች ምድር ናት›› ያሏት በሸዋልኢድ፤ ክብረ በዓል ላይ የታደሙት የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናንሲሴ ጫሊ፤ ታይተው የማይጠገቡ፣ ከእኛ አልፈው ዓለምን የሚያስደምሙና ቀልብን የሚገዙ ውብ የቱሪዝም ሀብቶች አሏት ሲሉ አመልክተዋል፡፡ ከእነዚህ ሀብቶች መካከል ዘመናትን የተሻገሩ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ፣ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ባህላዊ ሀብቶች በብዛት መገኘታቸው ኢትዮጵያ የብዝሃነት ተምሳሌት እና የውብ ባህሎች ባለቤት መሆኗን የሚያስረግጥ እውነት ነው ብለዋል፡፡

ሚኒስትሯ እድሜ ጠገቧ የሀረር ከተማ ለዚህ አይነተኛ ማሳያ እንደሆነች ጠቅሰው፤ በውስጧ ታሪካዊ አሻራዎችን፣ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ እሴቶችን አምቃ የያዘች ሙዝየም እንደሆነች አስረድተዋል፡፡

ከተማዋ የቀደምት ስልጣኔ ባለቤትና የሃይማኖት ማዕከል እንደመሆኗ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወራረዱ የመጡ ትውፊታዊ መገለጫዎችና ቱባ ባህሎች ዛሬም ቢሆን የሚንፀባረቁባት እንደሆነች ይገልፃሉ፡ ፡ በተጠናቀቀው ሳምንት የተከበረው የሹዋልኢድ ፌስቲቫልም ከዚህ የባህልና ሃይማኖት ምንጭ የሚቀዱ እሴቶች መካከል አንዱ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

‹‹ሹዋልኢድ የታላቁን የረመዳን ወር መጠናቀቅን ተንተርሶ የሚከናወን እና በሀረር ህዝብ የሚከበር ደማቅ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ነው›› የሚሉት አምባሳደር ናንሲሴ ጫሊ፤ ወቅቱ የረመዳን ወር መጠናቀቅን ተከትሎ የሀረር ከተማ ሞገስና ልዩ መለያ የሆነው የጀጎል ግንብ በሸዋልዒድ ክብረ-በዓል የሚያሸበርቅበት፣ ስሜትን የሚቆጣጠሩ ትዕይንቶች የሚከወኑበት፣ ሀረር ከወትሮው በተለየ መልኩ የምትፈካበት፣ የፍቅርና የእንግዳ ተቀባይነት ምልክት የሆነው የሀረር ህዝብ በቱባ ባህሉ የሚደምቅበት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለፃ፤ በመንፈሳዊ መዝሙሮችና ውዝዋዜዎች ተጀምሮ በቅዱሳን መፅሐፍት ንባብ ተዋጅቶ በምርቃትና መልካም ምኞቶች የሚቋጨው ሹዋልዒድ በውስጡ ከኢትዮጵያ አልፎ ለዓለም ህዝቦች ፋይዳ ያላቸው እሴቶችን መያዙንም ጠቁመዋል፡፡ ይህ መሆኑም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት በዓለም የማይዳሰሱ ቅርሶች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት እና የዓለም ህዝቦች ሁሉ ሀብት እንዲሆን አስችሎታል ብለዋል፡፡

ይህን ሃይማኖታዊ ሁነት በዓለም የማይዳሰስ ቅርስነት እንዲመዘገብ ያስቻሉ አንኳር ጉዳዮችን የሚያነሱት አምባሳደር ናንሲሴ ጫሊ፤ የመጀመሪያው ሸዋልዒድ ፆታ ሳይለይ በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ የማህበረሰብ አባላትን በአንድነት የሚያስተሳስር እና የእድሜ ባለፀጋዎች ለቀጣዩ ትውልድ እውቀትና ልምድ የሚያጋሩበት ሥርዓት መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ወጣቶች የራሳቸውን ባህልና ወግ እንዲያውቁ፤ በቤተሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ ለቀጣዩ ትውልድ አስተምህሮቶች የሚሰርፁበት እንዲሁም ስነ-ስርዓቱ የሚካሄዱባቸው ስፍራዎች ጭምር በቅርስነት የሚጠበቅበትን ሁኔታ የሚያወርስ ሃይማኖታዊ እሴት በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡



ፎቶ፡-ብርሃን ታደሰ

የዘንድሮው የሸዋሊድ በዓል በሀረር ከተማ በደማቅ ሥነ ሥርዓት ተከብሯል

ሚኒስትሯ እንዳስታወቁት፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ ወደርየለሽ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ የቱሪዝም ሀብቶች ባለቤት እንደመሆኗ ለቱሪዝም ልማትእምቅ አቅም አላት፡፡ እነዚህን ፈርጀ ብዙና መጠነ ሰፊ የቱሪዝም ሀብቶች አልምቶ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም በማስተዋወቅ የጎብኝዎችን ፍሰት ማሳደግ ይገባል፡፡ ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥም ያስፈልጋል፡፡

ለዚህም መንግሥት የቱሪዝም ዘርፍን ከኢትዮጵያ የእድገትና የብልፅግና መሰረቶች መካከል አንዱ በማድረግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ላይ እንደሚገኝ ሚኒስትሯ አስታውቀዋል፡፡ ሚኒስትሯ ኢትዮጵያዊያን በተለይም ይህን ሃይማኖታዊ ሀብት ጠብቆና ተንከባክቦ በትውልድ ቅብብሎሽ ለዚህ ክብር ላበቃው የሀረሪ ህዝብ ምስጋና እንደሚገባውም ገልጸዋል።

የሸዋልኢድ በዩኔስኮ በዓለም የማይዳሰስ ቅርስነት መመዝገቡ ቀደም ብሎ በሚዳሰስ ቅርስነት ከተመዘገበው የጀጎል ግንብ ጋር ተዳምሮ ለሀረር ልዩ ገፅታን እንደሚያጎናፅፋትና የቱሪስት መዳረሻነቷንም በይበልጥ እንደሚያሰፋው ይናገራሉ፡፡ እንደ ሀረር ያሉ የቱሪዝም ፀጋዎች ማዕከላት በቱሪዝም መሰረተ ልማትና በቱሪስት ፋሲሊቲዎች እንዲጠናከሩ በማድረግ እና ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ ተመራጭና ተወዳዳሪ የቱሪስት መዳረሻዎች ማድረግ ቀዳሚ ትኩረት እንደሚያስፈልግም ያስገነዝባሉ፡፡ እንደ ሸዋልኢድ ያሉ በሀረሪ ክልል የሚገኙ የቱሪዝም ሀብቶችን በማልማትና በማስተዋወቅ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ከማድረግ አንፃር ቱሪዝም ሚኒስቴር ከክልሉ መንግሥት ጋር በትብብር እንደሚሰራም አረጋግጠዋል፡፡

የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ የሀረሪዎች የጥበብና የእውቀት ውጤቶች ድንበር ተሻግረው የዓለም ህዝቦች የቅርስ ሀብት መሆናቸውን ይገልፃሉ። ሀረሪዎች ከደማቅ ታሪኮቻቸው ጎን ለጎንም የሰላምና የፍቅር ተምሳሌት መሆናቸውን ይናገራሉ።

‹‹በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በዓለም በማይዳሰስ ቅርስነት የተመዘገበው የሸዋልኢድ በዓል የፍቅር በዓል ነው›› የሚሉት ሚኒስትሩ፤ አኩሪ ባህሎቻችንና ቅርሶቻችንን በመንከባከብ፣ በመጠበቅና ለትውልድ ለማስተላለፍ በሚከናወኑ ስራዎች ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በጋራ መስራት እንደሚጠበቅባቸውም ያስገነዝባሉ።

የሸዋል ኢድ በዓል በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና የትምህርት ተቋም (ዩኔስኮ) በዓለም የማይዳሰስ ቅርስነት ህዳር ወር 2016 ዓ.ም ነበር የተመዘገበው። በዓሉ በዩኔስኮ ከተመዘገበ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀናት ተከብሮ ማለፉ ይታወሳል።

በተለያዩ ስርዓቶች በሀረር ከተማ በድምቀት የተከበረው የሸዋል ኢድ በዓልን ለማስተዋወቅ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ኤሊያስ ሽኩር በሰጡት ማብራሪያ፤ በዓሉ ባህላዊ ይዘቶቹን ጠብቆ እንዲጎለብትና ለአካባቢው ተጨማሪ የቱሪስት መስህብ እንዲሆን ወደ ሥራ መገባቱን ይናገራሉ። ለዚህም ከሀረሪ ክልል አስተዳደርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ የሀረሪ ማህበረሰቦች ለቅርስ የሚሰጡት ትኩረትና ትርጉምም ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን ያስረዳሉ።

እንደ ኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን መረጃ የሸዋል ኢድ በዓልን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጎብኝዎች በይበልጥ ለማስተዋወቅም በሀረር ከተማ አራት ሙዚየሞች ተመርጠው የተለያዩ ዝግጅቶችና የቅርስ ልማት ስራዎች እየተከናወኑ ነው።

ጥንታዊቷ የሀረር ከተማ የበርካታ ቅርሶች መገኛ በመሆኗ በርካታ ቱሪስቶች ለጉብኝት ወደ ስፍራው እንደሚያቀኑ በተለያዩ ጊዜዎች የወጡ መረጃዎች ያመለክታሉ። በመሆኑም የሸዋልኢድና ሌሎች ቅርሶች በአግባቡ ተጠብቀው እንዲጎለብቱና ለቱሪዝም ዘርፉ ያላቸው አበርክቶ እንዲያድግ ትኩረት መስጠቱን የቱሪዝም ሚኒስቴር እንዲሁም የሀረሪ ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ እየገለፁ ይገኛሉ።

ሸዋልኢድ የሚከበርባት ሀረር የጥንታዊት ኢትዮጵያ የሥልጣኔ ማሳያ ተብላ የምትጠቀስ ሲሆን፣ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በወቅቱ ሀረርን ያስተዳድሯት የነበሩት አሚር ኑር ከተማዋን ከጥቃት ለመከላከል የገነቡት የጁገል ግንብ በዓለም ቅርስነት ተመዝግቧል። ይህ ቅርስ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ተቋም እ.ኤ.አ በ2006 የተመዘገበ ሲሆን፣ አምስት በሮች እንዳሉት ይታወቃል። በ7ኛው ክፍለ ዘመን እንደተቆረቆረች የሚነገርላት ጥንታዊቷ ሀረር በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡትን የጀጎል ግንብ እና የሸዋል ኢድ በዓልን ጨምሮ የበርካታ የመስህብ ስፍራዎች መገኛም ነች።

ኢትዮጵያ የባህል፣ የታሪክ፣ የተፈጥሮና የቅርስ ሀብቶች በስፋት ከሚገኙባቸው ቀዳሚ ሀገራት ተርታ ትመደባለች። ይሁን እንጂ እነዚህን ሀብቶች በሚፈለገው መጠን የማስተዋወቅ፣ የማልማትና ከሀብቱ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ አቅም ግን አሁንም ድረስ እንዳልጎለበተ ይታመናል። ይህን እክል ለመቅረፍ መንግሥት የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ነድፎ እየሠራ መሆኑን በተለያዩ መድረኮችና መንገዶችም ሲገለፅ ይሰማል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የኮሪያ ዘመቻ

**ዋስልኝ አየለ**

### ሄዶ ከኮሪያ ዘማች ሲመለስ ያወሳል ናፍቆቱን በክራሩ ድምጽ

ብሏል ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ):: ‹‹የኮሪያ ዘማች›› የሚለው ቃል በትልልቅ አዛውንቶች ዛሬ ድረስ ይነገራል:: በወቅቱ የ7 ዓመት ልጅ የነበረ እና ዛሬ የ80 ዓመት አዛውንት የሆነ ሰው ክስተቱን ያስታውሳል ማለት ነው:: በኢትዮጵያ የሰላም ማስከበር ታሪክ ውስጥ ተደጋግሞ ስሙ ይነሳል:: በታሪክ ሰነዶችና በታሪክ ሰዎች ብቻ ሳይሆን በዜናዎችና ትንታኔዎችም የዲፕሎማሲ ቋንቋ ጭምር ሆኖ ያገለግላል:: ይህ የኢትዮጵያውያን የኮሪያ ዘመች ታሪክ ነው::

በዚህ ሳምንት ከምናስታውሳቸው የታሪክ ክስተቶች አንዱ ከ73 ዓመታት በፊት የተከሰተው የኮሪያ ዘማች ታሪክ ነው:: የኮሪያ ዘማች ትውስታ ባለክራሩን የሙዚቃ አርበኛ ካሳ ተሰማን አስከትሎ ወደ ኮሪያ የሄደው የኢትዮጵያ አርበኞች ታሪክ ነው:: በስሙ የተሰየመ ፓርክ አፍንጮ በር አጠገብ እንዳለ ልብ ይሏል::

የኮሪያ ዘመቻ ከሚያዚያ 8 ቀን 1943 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ ሳምንት የተከናወነ ነበር:: 2 ሺህ 168 ወታደር ያሰለፈው የኢትዮጵያ የክቡር ዘበኛ ሠራዊት፣ ቃኘው የሻለቃ ጦር ወደ ኮሪያ ዘመተ። ከዘማቾቹ መካከል አንዱ የነበረው ‹‹የክራሩ ጌታ›› 50 አለቃ ካሣ ተሰማ ይገኝበታል:: ‹‹እልም አለ ባቡሩ›› በሚለው ዘፈኑም ክስተቱን ለታሪክ አስቀምጦታል::

የመጀመሪያው ዙር የኮሪያ ዘማቾች አንድ ሺህ 153 ሲሆኑ፤ ቀኑ ግን በትክክል አልተገለጸም:: አብዛኞቹ መረጃዎች የሚያሳዩት በመጋቢት ወር መጨረሻ አካባቢ መሆኑን ነው:: የኢትዮጵያ ፕሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ከአምስት ዓመት በፊት በሰራው ዘገባ መጋቢት 30 የሚል አለው:: ምናልባት እሱ የመጀመሪያው ከሆነ የሚያዝያ ስምንትና ዘጠኝ አካባቢ ያለው ሁለተኛው ዙር ይሆናል ማለት ነው:: ያም ሆነ ይህ የኮሪያ ዘማቾች በዚህ ሳምንት ይታወሳል ማለት ነው::

የኮሪያ ዘማች እና ከኮሪያ ዘማቾች ማህበር መሥራች አንዱ የሆኑት የማህበሩ ፕሬዚዳንት ኮሎኔል መለሰ ተሰማ፣ በተመሳሳይ ከዘማቾች አንዱ የሆኑት አስር አለቃ ዘነበወርቅ በላይነህ የኮሪያ ዘማቾች 60ኛ ዓመት ሲከበር ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገው ነበር::

ዘማቾቹ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ዘመቻው በአምስት ዙር ነበር:: በአጠቃላይ ከስድስት ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች የዘመቱ ሲሆን 122 የሚሆኑት ተሰውተዋል:: ከኢትዮጵያ ወታደሮች አንድም የተማረከ አልነበረም፤ ‹‹ሬሳ እንኳን አልተማረከብንም›› ይላሉ ዘማቾቹ::

በ2005 ዓ.ም የኮሪያ ጦርነት 60ኛ ዓመት ሲዘከር ዓለም አቀፉ የሚዲያ ተቋም ቢቢሲ ‹‹ኢትዮጵያዊው ጀግና በኮሪያ ጦርነት›› በሚል ርዕስ የኮሪያ ዘማች ስለነበሩት ሌተናል ማሞ ሀብተወልድ ሰፊ ሐተታ አስነብቧል:: በዚህም የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት ለዓለም አሳውቋል:: የቢቢሲ ዓለም አቀፍ ሐተታ የመግቢያው ጽሑፍ ደመቅ (Bold) ተደርጎ እንዲህ ተጽፏል::

‹‹ከ60 ዓመታት በፊት፤ ኢትዮጵያ ጦርነት ላይ ነበረች:: ጦርነቱ አፍሪካ ውስጥ እንዳይመስላችሁ! ይልቁንም በሺዎች የሚቆጠር ማይል ርቀት ላይ ኮሪያ ውስጥ ነው…›› እያለ ይቀጥላል::

ቢቢሲ በዚያው ሐተታው እንደገለጸው፤ ኢትዮጵያውያን በኮሪያ 253 ውጊያዎችን (battles) አድርገዋል:: ‹‹በጦር ሜዳ እጅ አንሰጥም!›› የሚል መሪ ቃል ነበራቸው:: መሪ ቃላቸውንም በተግባር አሳይተዋል::

እነሆ ኢትዮጵያም በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለምም ሰላም በማስከበር እንድትታወቅ አደረጋት:: እነዚህ የኮሪያ ዘማች ጀግኖችም ሲታወሱ ይኖራሉ::

### በልደቱም፣ በሞቱም፣ በዘፈኑም የበዓል አድማቂው የሙዚቃ ንጉሥ

የዚህ ሰው ነገር ይገርማል! ከውልደቱ ይጀምራል:: የተወለደው በዕለተ መስቀል መስከረም 17 ቀን ነው:: ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ደግሞ የፋሲካ በዓል ዕለት ሚያዚያ 11 ቀን ነው:: የዚያን ዓመት የፋሲካ በዓል በሀዘን ድባብ የተዋጠ እንዲሆን አድርጎታል:: በዘፈኑ ደግሞ በዓላትን ሲያደምቅ ኖሯል:: በሕያው ሥራው የወደፊት በዓላትንም ያደምቃል:: ይህ ሰው የሙዚቃው ንጉሥ የክብር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ነው::

**ከእስር በኋላም ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ በእንደዚህ ያለ ተግባር ላይ እንዳይሰማሩ ከፍተኛ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም፤ ማስፈራሪያው ሳይበግራቸው አርበኞችን በግጥምና ወኔ ቀስቃሽ ጽሑፎች በማበረታታት፣ መረጃ በማቀበል፣ መሣሪያ በማዳረስ የጀግንነት ተግባር ፈጽመዋል**

ጥላሁን ገሠሠ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ከ15 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሚያዚያ 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፋሲካ በዓል ዕለት ነው:: የፋሲካ በዓል ቀኑ ስለሚቀያየር በየዓመቱ ሚያዚያ 11 አይሆንም:: የ2001 ዓ.ም የፋሲካ በዓል የተከበረው በጥላሁን ገሠሠ ሞት ሀዘን ነው:: ያም ሆኖ ግን የጀግና ሞት ሀዘን አይደለምና መገናኛ ብዙኃንን ለአንድ ሳምንት ያህል በአንድ ጉዳይ ብቻ አድምቆ ይዞ ቆይቷል:: ሥርዓተ ቀብሩም የተፈጸመው ለሳምንት ያህል ሰፊ ሽፋን ከተሰጠው በኋላ ነው::

የ15ኛ ዓመት የጥላሁን ገሠሠን የሙት ዓመት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ ከሕይወትና ሥራዎቹ ጥቂቶችን እናስታውስ::

ጥላሁን ገሠሠ ከእናቱ ከወይዘሮ ጌጤ ጉሩሙ እና ከአባቱ ከአቶ ገሠሠ ንጉሤ በአዲስ አበባ ልዩ ስሙ ጠመንጃ ያዥ እየተባለ ከሚጠራው ሰፈር መስከረም 17 ቀን 1933 ዓ.ም የመስቀል ዕለት ተወለደ። ዕድሜው 14 ዓመት እንደሆነ ከአያቱ ጋር እንዲኖር ወደ ወሊሶ ተወሰደ፤ ራስ ጎበና በሚባለው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርት ጀመረ።

በትምህርት ቤት ሳለ፤ ጥላሁን ከፍተኛ የሆነ የሙዚቃ ፍቅር እያሳየ መጣ። አያቱ ግን ትኩረቱን በሙሉ በትምህርቱ ላይ እንዲያደርግ ይመክሩት ነበር። የራስ ጎበና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተዳዳሪ የነበሩት ሱዳናዊው አቶ ሼዳድ ደግሞ የጥላሁንን የሙዚቃ ፍቅር በማየት ወደ ሱዳን እንዲሄድና በዚያም ሙዚቃ እንዲያጠና ይመክሩት ነበር። ጥላሁን ወደ ሱዳን ባይሄድም ምክራቸውን ግን ትልቅ ቦታ ሰጥቶት ነበር።

ከሀገር ፍቅር ቲያትር ንጋትዋ ከልካይ እና ኢዮኤል ዮሐንስ ሌሎችም የሀገር ፍቅር ተዋንያን በትምህርት ቤታቸው ትርኢት ሊያሳዩ በመጡ ጊዜ፤ ይህን እድል በመጠቀም ጥላሁን ለሙዚቃ ያለውን ፍቅር ኢዮኤል ጋር ባደረገው ውይይት በሙዚቃ መግፋት ከፈለገ ወደ አዲስ አበባ መሄድ እንዳለበት መከሩት። ጥላሁን ትምህርቱን አቋርጦ ጉዞውን ወደ አዲስ አበባ አቀና። ኩብለላውን በእግር የጀመረው ለአያቱ ሳይነግር ስለነበር ከቤት ሲጠፋ አያቱ ለአጎቱ ሁኔታውን በመንገር ጥላሁንን ይጠብቁ ጀመር። ጥላሁንም የአሥራ አምስት ኪሎ ሜትር መንገዱን ጨርሶ ቱሉ ቦሎ ደረሰ፤ ከዚያም ከአክስቱ ከወይዘሮ ተመኔ ባንቱ ቤት አድሮ ወደመጣበት ወደ ወሊሶ አያቱ ዘንድ ተይዞ ተመለሰ ።

በሙዚቃ ፍቅር በጣም የተቃጠለው ጥላሁን አያቱ ቤት አንድ ቀን ብቻ በማደር ጉዞውን እንደገና ወደ አዲስ አበባ አቀና፤ በዚህ ጊዜ ግን በጭነት መኪና ላይ በመንጠልጠል ነበር። ጥላሁን አዲስ አበባ እንደገባ በሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ተቀጠረ። በዚያም ጥቂት አመታት ከሰራ በኋላ ወደ ክብር ዘበኛ ባንድ በመቀላቀል እነሆ ታዋቂና ዝነኛ ለመሆን በቃ።

በ1953 ዓ.ም የታኅሳስ ግርግር ትልቅ ችግር ውስጥ ወድቆ ነበር ። ለጥቂት ጊዜም ታስሮ ተፈቷል። ከዚያም ወደ ቀድሞው ሀገር ፍቅር በመመለስ ተወዳጅና ታዋቂ ለመሆን በቅቷል። ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ሀገር ፍቅር ቲያትር ቤትን በጎበኙበት ጊዜ ሦስት ጊዜ ወጥቶ ዘፍኗል፤ ንጉሡ ነገሥቱም ‹‹ጥሩ ድምጽ አለህ፤ እንዳታበላሸው›› የሚል አስተያየትም እንደሰጡት ይነገራል ።

ከጥላሁን ዘፈኖች አብዛኞቹ የአማርኛ ሲሆኑ፤ የተወሰኑ ዘፈኖችን ደግሞ በኦሮምኛ እና በሱዳንኛ ዘፍኗል። ጥላሁን ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ላደረገው አስተዋጽኦ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ተሰጥቶታል:: ከኢትዮጵያ ኪነጥበብና የብዙኃን መገናኛ ሽልማት ድርጅት የሙሉ ዘመን ሽልማት ተሸላሚ ሆኗል::

ትንፋሼ ተቀርጾ ይቀመጥ ማልቀሻ
ይህ ነው የሞትኩለት የኔ ማስታወሻ።
ውበቷን ሳሞግስ የለምለም ሀገሬን
ማንም አይዘነጋም በጩኸት መኖሬን!
ዜማ እንጉርጉሮዬም የግሌ ቅላጼ
ተቀርጾ ይቀመጥ ታሪኬ ነው ድምጼ።
ያስቀየምኩት ቢኖር የጠላኝ በቁሜ
ድምጼን ሰምቶ ያዝናል ለረገፈው አጽሜ።
እኔን ለበደሉኝ ሰርዣለሁ ቂሜን
በኔም የከፋችሁ ይቅር በሉት አጽሜን!

### ስንዱ ገብሩ

ሌላኛዋ የዚህ ሳምንት ክስተት ስንዱ ገብሩ ናት:: ከ15 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሚያዚያ 12 ቀን 2001 ዓ.ም (ጥላሁን ገሠሠ ባረፈ በነጋታው ማለት ነው) ታዋቂዋ አርበኛ እና ደራሲ ስንዱ ገብሩ አረፈች:: የዚያን ዓመት ፋሲካ እንዲህ አይነት አጋጣሚዎችን ያስተናገደ ነበር ማለት ይቻላል:: ለብዙ ሴቶች አርዓያ የሆነችውን ስንዱ ገብሩ ታሪክም በጥቂቱ እናስታውስ::

የክብር ዶክተር የሆኑት ወይዘሮ ስንዱ ገብሩ የተወለዱት ጥር 6 ቀን 1908 ዓ.ም በቀድሞው አጠራር በሸዋ ክፍለ ሀገር በመናገሻ አውራጃ በአዲስ አለም ከተማ ነው:: አባታቸውም ታዋቂው ዲፕሎማት፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት እና የጎንደር ከተማ አስተዳዳሪ የነበሩት ከንቲባ ገብሩ ናቸው::

ስንዱ እድሜአቸው ለትምህርት በደረሰበት ወቅት ከቤታቸው አስተማሪ ተቀጥሮላቸው የአማርኛን ትምህርት ከፊደል መቁጠር እስከ ዳዊት መድገም በቤታቸው ተምረዋል። ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ሄደው በስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት በመግባት እስከ ስምንተኛ ክፍል ተምረዋል።

አባታቸው ከንቲባ ገብሩ፤ ስንዱን እያስከተሉ ወደ ቤተ መንግሥትም ሆነ ሌላ ሥፍራዎች ይወስዷቸው እንደነበረና ከጊዜው አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ጋር እንዳስተዋወቋቸው ስለ ስንዱ የተጻፉ ሰነዶች ያሳያሉ:: አልጋ ወራሹም የወጣቷን ብልህነትና ትጋት በማድነቅ ወደ ፈረንጅ ሀገር ተልከው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ባዘዙት መሠረት ወይዘሮ ስንዱ በ1921 ዓ.ም ወደ ስዊስ ለትምህርት ቢሄዱም ኑሮው ስላልተመቻቸውና ትምህርት ይሰጥበት የነበረውን የጀርመንኛ ቋንቋ ስላልወደዱት ወደ ፈረንሳይ አቅንተው ትምህርታቸውን ተከታትለዋል።

በመጨረሻም በስዊስ እና በፈረንሳይ ሁለት ትምህርት ቤቶች በመዘዋወር በዲፕሎማ ተመረቁ። እዛው የሕግ ትምህርት ለመቀጠል ጀምረው የነበረ ቢሆንም፤ ፍላጎታቸው ወደ ሥነ ጽሑፍ በማዘንበሉ በአጠቃላይ ለአምስት ዓመታት እዚያው ተምረው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ።

የጣሊያን ፋሺስቶች ኢትዮጵያን በወረሩ ጊዜ ወይዘሮ ስንዱ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እና ሆለታ ውስጥ ከሚገኙ ወደ መቶ የሚጠጉ የጦር መኮንኖች ጋር ተቀላቅለው ፋሺስቶችን ለመፋለም ወደ ቦሬ ሄዱ። እዚያም የመትረየስ አተኳኮስ ትምህርት ተማሩ። ወደ ነቀምት በመሄድም ሕዝብን እየሰበሰቡ ስለ ነፃነት ማስተማሩን ተያያዙት። በዚህ ወቅት በባንዳዎች ጠቋሚነት በፋሽስት እጅ ከመውደቅ ለጥቂት አምልጠው ጎሬ ላይ ከልዑል ራስ እምሩ ጦር ጋር ተቀላቀሉ። ከዚያም በጦርነቱ የሚጎዱ አርበኞችን ለማከም የሚሆን ቀይ መስቀል ለማቋቋም መፈለጋቸውን ለራስ እምሩ አማክረው በተሰጣቸው 500 ብር አቋቁመው አርበኞችን መርዳት ጀመሩ። ወዲያው ግን እርሳቸው ተቀላቅለውት የነበረው የጥቁር አንበሳ ጦር ሲመታ በጣልያን ሠራዊት እጅ ተማርከው በእስር ወደ አዲስ አበባ አምጥተዋቸው የቁም እስረኛ ሆነዋል።

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ግራዚያኒን ለመግደል በተደረገው ሙከራ ወንድማቸው መሸሻ ገብሩ አሉበት በመባል ይታሰሱ ስለነበር ወንድማቸውን ከአደጋ ለማዳን ሲሞክሩ ወይዘሮ ስንዱ በድጋሚ በፋሺስቶች እጅ ወደቁ። በወቅቱ ግራዚያኒ ይኖርበት የነበረው የገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ውስጥ ታሰሩ። ቀጥሎም ወደ አስመራ፣ ከዚያ ወደ ምጽዋ ተወሰዱ። ከምጽዋ ወደብ ሦስት መቶ ወንዶችና ስምንት ሴቶች (እማሆይ ጽጌ ማርያምን ጭምር) ሆነው በመርከብ ‹‹አዚናራ›› ወደተባለች የኢጣሊያኖች እስር ቤት ተወስደው ዘጠኝ ወራት ታሰሩ።

ከእስር በኋላም ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ በእንደዚህ ያለ ተግባር ላይ እንዳይሰማሩ ከፍተኛ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም፤ ማስፈራሪያው ሳይበግራቸው አርበኞችን በግጥምና ወኔ ቀስቃሽ ጽሑፎች በማበረታታት፣ መረጃ በማቀበል፣ መሣሪያ በማዳረስ የጀግንነት ተግባር ፈጽመዋል።

ከድል በኋላ ወይዘሮ ስንዱ ለሁለት ዓመታት ደሴ ከተማ የሚገኘው የወይዘሮ ስኂን ትምህርት ቤት አስተዳዳሪ በመሆን፣ በኋላም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰውም የእቴጌ መነን ትምህርት ቤት ምክትል ርዕሰ መምህርነት፣ ከዚያም የመጀመሪያዋ ሴት ርዕሰ መምህር ሆነው አገልግለዋል። በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት በነበሩበት ወቅት፤ ‹‹ኮከብ ያለው ያበራል ገና››፣ ‹‹የየካቲት ቀኖች››፣ ‹‹የኑሮ ስህተት›› የሚሉ ትያትሮችን ሠርተው አቅርበዋል።

ወይዘሮ ስንዱ ከ1948 ዓ.ም እስከ 1952 ዓ.ም ድረስ የመጀመሪያዋ የሴት የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባልና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ምክትል ሊቀ መንበር ሆነው አገልግለዋል። በዚህ ምክር ቤት አባል በነበሩበት ጊዜ ብቸኛዋ ሴት ከመሆናቸውም ባሻገር የሴቶች እኩልነት በማይከበርበት ጊዜ እና ‹‹የወንድ ዓለም›› በገነነበት የታሪክ ምዕራፍ የሴቶችን ሰብዓዊ መብት ለማስከበርና እኩልነትን በሕግ ለማስተማመን ብዙ የታገሉ ሴት ነበሩ።

ስንዱ ገብሩ ከተሳተፉባቸው ጥቂቶችን እንጥቀስ

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ማኅበር ፕሬዚዳንት፣ የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ዋና ፀሐፊነትና አስተዳዳሪነት፣ በምዕራብ ጀርመን ለሦስት ዓመት የትምህርት አታሼ ሆነው አገልግለዋል::

ከመጽሐፎቻቸው ደግሞ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::

ኮከብህ ያውና ያበራል ገና፣ በግራዚያኒ ጊዜ የየካቲት ቀኖች (1947 ዓ.ም)፣ የታደለች ህልም (1948 ዓ.ም)፣ ርእስ የሌለው ትዳር (1948 ዓ.ም)፣ የኔሮ ስህተት (1948 ዓ.ም)፣ ከማይጨው መልስ (1949 ዓ.ም)፣ ፊታውራሪ ረታ አዳሙ (1949 ዓ.ም) እና የመሳሰሉት ሌሎች ጽሑፎቻቸው ይጠቀሳሉ::

የመጀመሪያዋ የሴት ፓርላማ አባል፣ የሴት የሰብዓዊ መብት ተሟጋች፣ ጀግና እና ፀረ ፋሺስት አርበኛ፣ ፀሐፊ ተውኔት፣ የመጽሐፍ ደራሲ፣ እና የመጀመሪያዋ የሴት ዲፕሎማት ስንዱ ገብሩ (የክቡር ዶክተር) ሚያዝያ 12 ቀን 2001 ዓ.ም በተወለዱ በ93 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ተለይተዋል:: ሥርዓተ ቀብራቸውም በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል::

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ጉምቱው ብዕረኛ!

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ብዕረኛውን ብዕር ያነሳዋል:: የሀገራችን የጥበብ ቤት ጭር ብሎና ሰው አልባ፤ ኦና ሆኖ አያውቅም:: በየዘመናቱ ሁሌም ቢሆን ብዕራቸውን እያነሱ በከተቡ ቁጥር “አቤት እንዴት ያለው ብዕረኛ ነው!” እያልን የምንደመምባቸው ዛሬም አሉ:: ይህኛው ዘመንም፤ በስነ ጽሁፉ የድርሻውን ይዞ ቆሟል:: በዛሬው የዝነኞች ገጻችን ከዚህኛው ዘመን የኪነ-ጥበብ ፈርጥ ከሆኑት መካከል ስለ አንድ ሰው የህይወት ታሪክ፣ ዘመን አይሽሬ ከሆኑ ስራዎቹ ጋር በማጣመር ልናቀርብላችሁ ወደናል። ይህ ሰው በሥራቸው የስነ-ጽሁፍ ስራዎቹ ከአንባቢያንና ሀያሲያን ዘንድ ትልቅ አድናቆትንና ዝናን የተቸረ፣ ድንቅ በሆኑ የፈጠራና በራሱ የአጻጻፍ ስልት ልዩ ልዩ ሽልማቶችን ማግኘት የቻለ ባለ ብዙ ተሰጥኦና ድንቅ አዕምሮ ባለቤት፤ ደራሲና ገጣሚ አዳም ረታ ነው። ከማንነቱ ጫፍ እስከ ብዕሩ መድረሻ፤ ከትናንቱ ተነስተን ዛሬን በዚህ ውስጥ እንፈልገዋለን::

ሀምሌ 8 ቀን 1950 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተወለደው አዳም ረታ ገና በልጅነቱ በውስጡ የተጸነሰው የስነ-ጹሁፍ ዝንባሌ ዛሬ ላበረከታቸው ተወዳጅ ስራዎቹ መሰረት ጥሎለታል። ስለ ሥራዎቹ በተነሳ ቁጥር ሁሌም የሚለው አለው:: በልጅነቱ ያሳለፈው ኪነ ጥበባዊ ጊዜ ለደረሰበት ትልቅ መሰላል ሊሆነው ስለመቻሉ ነው:: በአንድ ወቅትም በ“አዲስ ነገር” ጋዜጣ ላይ በሰጠው ቃለ መጠይቅም እንዲህ የሚል ነበር፤ 5ኛ ክፍል እያለሁ አርብ አርብ ከሰአት በኋላ ሪፖርት እናቀርባለን:: ደንቡ ከጋዜጣ ያነበብነውን ወይም ከሬዲዮ የሰማነውን ነገር በራሳችን አማርኛ አሳጥረን ጽፈን ክፍል ውስጥ ማቅረብ ነው:: ሁልጊዜ ርእስ የሚሆኑት የጃንሆይ ጉብኝት ፤ የአዲስ አበባ አንደኛ ዲቪዚዮን እግር ኳስ ውድድር ውጤት እና የመካከለኛው ምሥራቅ ግጭት ነው:: ነገር ግን ይህን መጻፍ ሰለቸኝ:: አንድ ቀን በመንገድ ላይ ስሄድ የዶሮ ነጋዴዎች ሀይለኛ አውሎ ነፋስ መጥቶ ሲያተራምሳቸው እና ዶሮዎቹ ከቅርጫት እየበረሩ ሲያመልጡ ነጋዴዎቹም እነሱን ለመያዝ የሚያደርጉትን መውደቅና መነሳት አየሁ እና ገረመኝ:: ያን ለመጻፍ ወሰንኩ:: ጽፌም ክፍል ውስጥ አቀረብኩና ተማሪዎቹን ትንሽ አስደሰትኳቸው:: ከዚያ መምህሩ ከየት አመጣኸው ሲሉኝ ከጋዜጣ አንብቤ ነው አልኩ:: ጋዜጣ ላይ እንዲህ አይነት ነገር አይጻፍም ብለው ጢሜን አበረሩኝ::ከዚያ ግን ለተማሪዎች አዳሙ ደራሲ ነው የሚሆነው ብለው ተናገሩ:: ደራሲ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያኔ አልገባኝም::” በማለት መነሻውን በትውስታ ያጋራል::

አዳም በአብዛኛው የሚጽፈውና ጉምቱነቱን የተቀዳጀው በልቦለዶች ቢሆንም ግጥሞችንም የመጻፍ ልዩ ችሎታ አለው። በእርግጥ ግጥሞቹን ሰብስቦ በመድብል ደረጃ ባያወጣቸውም፤ ነገር ግን በተለያዩ ጊዜያት በመፅሔቶች ላይ መታተም ችለዋል:: ከእርሱ ዘንድ ብቻ ተሸሽገው ያሉ በርካታ ያልታተሙ ግጥሞችና የስነ-ጽሁፍ ስራዎቹም እንዳሉት ይናገራል። “ታዲያ ምን ትጠብቃለህ አዳም?” ያስብላል፤ እንዲህ እንደ እርሱ ያሉ የብዕር ጠብታዎች ሲባክኑ መልካም አይደለምና:: በስነ-ጽሁፉ ብቻ ሳይሆን በቀለም ትምህርቱም የተሻለ ደረጃ ላይ መድረስ የቻለው አዳም ረታ በጂኦግራፊ የመጀመሪያ ዲግሪውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተቀበለ ሲሆን፤ ሁለተኛ ዲግሪውን ደግሞ በውጭ ሀገር አግኝቷል።

አዳም ረታ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ተሰጥኦው እንደ ሻማ ያበራበትና የብርሃን ችቦውን የለኮሰበት ጊዜ ነበር:: በ1977ዓ.ም፤ በኢትዮጵያ የስነ-ጽሁፍ ተከታዮች እና አንባቢያን ልብ ውስጥ የመሠረት ድንጋይ ያስቀመጠበትን የበኩር ስራውን ይዞ በአንዲት መጽሐፍ ብቅ አለ። ይሄውም “አባ ደፋር እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች” የተሰኘው መጽሐፍ ነው። በዚህ የአጫጭር ታሪኮች ስብስብ ውስጥ የተለያዩ ጸሐፊዎች የተሳተፉበት ሲሆን፤ ደራሲ አዳም ረታ ድብድብ፣ ዕብዱ ሺበሺ፣ ሲሮኮ እና ሲፊንክስ በድምሩ አራት ስራዎችን በመጽሐፉ ውስጥ ለማካተት ችሏል። በ1990 ዓ.ም “ጭጋግና ጠል” የአጭር ታሪኮች ስብስብ ውስጥ “ዘላን” የተሰኘ ልቦለዱ ታትሟል። እነዚህ ሁለቱ ከሌሎች ደራሲዎች ጋር፤ በጥምረት የታተሙለት በመሆኑ እንደ ወጥ ሳይቆጠሩ ቀርተዋል።

ደራሲው የመጀመሪያ ወጥ የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ የሆነውን “ማህሌትን” ለመጀመሪያ ጊዜ በ1981ዓ.ም ለማሳተም በቅቷል። ሌላው በሻማ ቡክስ በ1997 ዓ.ም የታተመው “ግራጫ ቃጭሎች” የሚለው መጽሐፉ ለአዳም ረታ ትልቅ የመሸጋገሪያ ድልድይና ልዩ ችሎታው የታየበት ወጥ ረጅም ልቦለድ ነው።

ጉዟቸውን የቀጠሉት የአዳም ረታ የማይነጥፉ የብዕር ጠብታዎቹ በ2001ዓ.ም አለንጋና ምስር እንዲሁም እቴሜቴ ሎሚሽታ በ2002 ዓ.ም ከሰማይ የወረደ ፍርፍር፣ በ2003 ዓ.ም ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ እና በ2004 ዓ.ም ሕማማት እና በገና በተከታታይ በየአመቱ ታትመው ለንባብ በቅተዋል። ከዚህ በኋላ ደግሞ መረቅ በ2007 ዓ.ም፣ የስንብት ቀለማት በ2008 ዓ.ም ሌላው በ2010 ዓ.ም አፍ የተሰኙ በርካታ ድንቅ ስራዎችን በተለየ አቀራረብ በመስራት ለአንባቢያን እነሆ ማለት ችሏል።

በአንድ ወቅት በ“አዲስ ነገር” ጋዜጣ ላይ በከተበው ጽሁፍ ስለራሱ ሲናገር በድግግሞሽና በአንድ አይነት መንገድ መሄድ በጣም እንደሚያሰለቸው ገልጾ ነበር። ለዚህ ደግሞ ስራዎቹን መመልከት ከቻልን ወጣ ያለና የራሱን የአቀራረብ ስልት ይዞ መምጣቱ ምስክር ነው።

ቀደም ሲል “በአባ ደፋርና ሌሎች ስብስቦች” ውስጥ ስራዎቹን የማቅረብ እድል በማግኘት የጀመረው አዳም ረታ የጥበብ ጉዞ ከስኬቶቹ ኋላ ቆየት ብሎም ሌሎች ወጣት ጸሐፊያን ፈለጉን ይከተሉ ዘንድ “አማሌሌ” በተሰኘው መጽሐፍ ላይ አብሯቸው በጥምረት ሰርቷል። ስራዎቹ በብዛት በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊና መሰል መስተጋብሮቻችን ውስጥ በሚገኙ ቀላል በሚመስሉ እምቅ ሃሳቦች ላይ የሚያጠነጥኑ ሲሆኑ፤ ኪናዊ ለዛን በተላበሰ መልኩ በጨዋታ እያዋዛ ልባችንን እንዲኮረኩሩን አድርጎ አቅርቧቸዋል። ቆም ብለን ደግሞ በጥልቀት እንድናስብና እራሳችንን እንድንመረምር ያደርገናል። የምናቡ ርቀትና ገለጻው፣ የሚያነሳቸው ሃሳቦችና የቋንቋ ሀብቱ ሁሌም አፍ ያስከፍታሉ::

አዳም ነዋሪነቱ በካናዳዋ ኦታዋ ይሁን እንጂ ሀገሩን በተመለከተ የምናብ ችግር የለበትም::እንዲያውም ከሌሎች ደራሲያን በተለየ የኢትዮጵያውያንን ሁለንተናዊ ገጽታ በድርሰቱ ውስጥ እስከ ጥቃቅኗ ቅንጣት ድረስ ወርዶ በዝርዝር ይተነትናል::በአንድ ወቅት ሀልዮ ከተባለ መጽሔት ጋር በነበረው ቆይታ ይህን ሲያስረዳ “ከሀገርህ ስትወጣ ራስህን ባዶ አድርገህ አይደለም የምትወጣው ሁሉን ነገር ትውስታህ ውስጥ ትይዛለህ” ብሏል::አክሎም “የትረካ ቅርጹን ነው እኔ የምፈጥረው እንጂ በውስጡ ሊነሱ የሚችሉ ግብረገባዊ እና ሌሎች ነገሮችን እኔ የምፈጥራቸው አይደሉም፤ አለም የሚሰጠኝ ነው::እኔ ህብረተሰቡ ውስጥ የምገኝ ቢሆንም በምጽፍ ጊዜ ግን ራሴን ነጥዬ ገለል ብዬ ለመመልከት እሞክራለሁ::”በማለት የአጻጻፍ መንገዱን ተናግሯል::


የብዕር ስራዎቹና ሃሳቦቹ እንደ ዓባይ ጅረት የማይነጥፉና ተቀድተው የማያልቁ ግዙፍ ባህር ናቸውና እስቲ ከሰራቸው ስራዎች መሀከል ከመጽሐፉ መጽሐፍ፣ ከገጽ ወደ ገጽ እየዘለልን በጥቂቱ እንቃኛቸው።

“ባዕዳን ከፋፍሎ ሊገዛህ ሲያሴር ካልገባህ እና እንደሰራህ ከተሰራህለት በአእምሮው ስፋት በለጠህ ማለት አይደለም? ለመሆኑ እግዚአብሔር ተፈጥሮንና ሰውን እንዴት ፈጠረው? በቃሉ ትዕዛዝ ነው። ሰው ሁን አለ ሰውም ሆነ። ዛፍ ሁን አለ፤ ዛፍም ሆነ ወዘተ...... ባዕዳን ተጣሉ ሲሉን መጣላት፣ ኑጡ ሲሉን መሮጥ፣ ራቁታችሁን ሁኑ ሲሉን መሆን፣ ሁሉ ነገራችን ከዚያም ዝቅ ያለ ነው። በተለይ በፖለቲካ ሳይንሱ። (የስንብት ቀለማት)

ይህ 960 ገጾችን የያዘው የስንብት ቀለማት መጽሐፍ ራሳችንን በደንብ እንድንመለከት ይጋብዘናል:: ከተወሰኑ ገጾች መሐከልም፡-

****

"የእኛ ሰፈር አዋቂ ይገርመኛል፤ ላባ አይቶ 'አሞራ አየሁ' የሚል፣ ጅና አይቶ 'አንበሳ አየሁ' የሚል፣ ጠብታ ውሃ አይቶ 'ዶፍ በዚህ አልፎ ነበር' የሚል፣ ቆዳ ቦት የሚያዘወትር ሰውዬ ቢያይ 'ወታደር አየሁ' የሚል ነው። (እነዚህን አይነቶች ፖለቲከኛ አያድርግብዎ!)






***

"የሚያስፈራኝ ደሃነትና የመንገድ መፍረስ አይደለም:: የሥጋና የአጥንቴ መድከም አይደለም:: የዕቃ መወደድ አይደለም:: እግዜር የከፈተውን አፍ ሳይዘጋው ካደረማ፤ እግዜሩም እግዜር እኔም ሰው አይደለሁም።

(የስንብት ቀለማት)

***

“ፍትህ ትወዳለህ፤ ፍትህ እንደጎደለ እያወቅህ ግን ዝም ትላለህ። አየህ ይሄ አንድ ሰው ሲከፋፈል ነው።”

***

“መኖር የሚከብደው ከሰው ጋር ብቻ አይደለም፤ ከዶሮም ጋር ነው። አሁን ከጎረቤቶቼ መጣላት ብፈልግ በ'ዶሮአችሁን ሰብስቡ' ሰበብ አምባጓሮ መቀስቀስ እችላለሁ። ዋናው እውነት መሆኑ አይደለም። ደፍሮ የመዘባረቅ ነው።”

(መረቅ)

“ዛሬ በትንንሽ ምሬት ይሞላና ጊዜ ይለወጣል።
ምንም የረባ ሳይደረግ ሰዎች ወዲያና ወዲህ ይራራቃሉ፣
የተያያዙ ይፈታታሉ፣
ፍቅር የገመዳቸው ይበታተናሉ።
ሁሌም ሚስጥር ነው።
ለምን እንደወደድንም ለምን እንዳልወደድንም ምስጢር ነው።”

(እቴሜቴ_ሎሚ_ሽታ)

****

“ጠዋት እዚህ ፀሐይ ስሞቅ የቆረጥኩት የአውራ ጣቴ ጥፍር ለስንት ጉንዳን እራት ይሆናል? ባላርስም አበላሁ ማለት ነው... ሂሂሂ”

***

“አብዮተኛ ውስጥ ቡርዧ አለ፣
ቡርዧ ውስጥ ፊውዳል አለ፣
ፊውዳሉ ውስጥ ገበሬ አለ፣
ገበሬው ውስጥ እረኛ አለ፣
እረኛ ውስጥ ላም አለ፣
ላሚ ውስጥ ሳር አለ፣
ሳሩ ውስጥ አፈር አለ::
ለሊታችን ተቆፍሮ ቢታይ ሁላችንም የምናልመው በእርግጥ አፈር ነው:: ታላቅ የመሰለው፣ የረቀቀ የመሰለው ፅንሰ ሃሳብ ሁሉ በምላስ ሙጫ የቆመ የአፈር እንክብል ነው።" (መረቅ)

****

“ይሄ ኅብረተሰብ እኔን ጎድቶኛል።
ቁስሌን መፍጠራቸውን ረስተውታል።
እኔ አልረሳሁትም።
አንድ ጥፊ ሲሰጡት ሌላ የሚጠብቅ
ወይ ጠንካራ ጉንጭ ያለው ነው፣
ወይ ጅል ቅዱስ ነው”

(ማህሌት)

*****

"አዕምሮአቸው ብሩህ ባህላቸው ግን የባርያ የሆኑ ስንት አሉ በእግዜር። ባላምንበትም ልማልበት።አይ አም ኢንተለጀንት ብሎ የሚናገር ግን ዘር ማንዘሩ በቁንጫ የሚበላበት፣ በጎጥ ብራንድ የነደደ ሰው አያበሽቅህም? በ'ነኝ' ሰው የሚበላለጥ ቢሆን የአለም ጌታዋ ብዙ ነበር። 'ውበት ሃሰት ነው ደም ግባትም ከንቱ ነው' እንደሚባለው አዕምሮም ሃሰት ነው ብልጥነትም ከንቱ ነው። ሁሉ ረጋፊ ነው።" (አፍ)

አዳም ረታ በተለየ የአጻጻፍ ስልቱ እና በስራዎቹ ጥልቀት ከአንባቢያንና የጥበብ አፍቃሪያን አድናቆትን ከማትረፉ ባሻገር ከሀገራችን ጉንቱ ሃያስያን ዘንድ አዎንታዊ ሂስ እና ምስክርነትን ማግኘት ችሏል።

ለምሳሌ ያህል ዳኛቸው ወርቁ ስለ አዳም ረታ ይህንን ብሎለታል፤ በ“አደፍርስ” የኢፒሶዲክ ሕግጋትን አጋምሶ ለማስተዋወቅ ከሞከረ ወዲህ በአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ በኢፒሶዲክ ተሟልቶ የተገኘ ድርሰት “ግራጫ ቃጭሎች” ነው። ... “ግራጫ ቃጭሎች” ከገፀ-ባህሪው አካልና ሥነ-ልቡና አሳሳል አልፈን ድንቅ ዓላማውን፣ ቋንቋውንና የሕይወት አተረጓጎሙን ስንመለከት የአዳም ረታ እውቀትና ልምድ ጠንከር - ጠጠር ብሎ በመዝገቡ በኩል ሲያስተጋባ ነው የምንመለከተው።...

ደራሲና ገጣሚ አዳም ረታ በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ሽልማቶችን ማግኘት የቻለ ሲሆን በዋናነት በ2009ዓ.ም

ኢስትዌስት ኢንተርቴይመንትና ኤቨንት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለመጀመሪያ ጊዜ ባዘጋጁት “ሆሄ” የሥነ ፅሑፍ ሽልማት ላይ በምርጥ የአመቱ ረዥም ልቦለድ ዘርፍ "የስንብት ቀለማት" በተሰኘው መጽሐፉ ተሸላሚ ለመሆን በቅቷል። የጉምቱውን ብዕረኛን ግሩም ቀለማትን በመቀየጥ በጥቂቱም ቢሆን ይችል ታህል ስንል፤ ነገም በማይነጥፉና በተሻሉ ህብረ ጥበባት ውስጥ እንደምናገኘው ተስፋ በማድረግ ነው::

# ዓለም አቀፍ

## የትራምፕ ጉዳይ በሚታይበት ፍርድ ቤት አቅራቢያ ራሱን ያቃጠለው ግለሰብ ሕይወት አለፈ

የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ የማጭበርበር ክስ በሚታይበት ማንሃታን በሚገኘው ፍርድ ቤት አቅራቢያ ራሱን ያቃጠለው ግለሰብ ሕይወት አለፈ። የ37 ዓመቱ ማክስዌል አዛሬሎ ተቀጣጣይ ፈሳሽ አርከፍክፎ ራሱን ከማቃጠሉ በፊት 'በሴራ የተሞሉ' በራሪ ወረቀቶችን በትኗል።

ይህ ክስተት ያጋጠመው የዶናልድ ትራምፕን ክስ ለመመልከት የሚሰሙ ዳኞች ምርጫ ከተጠናቀቀ በኋላ ነበር። ትራምፕ የዳኞችን ምርጫ ለመታደም በሕንጻው ውስጥ የነበሩ ሲሆን ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ሕንጻውን ለቀው ወጥተዋል።

ግለሰቡ ለሕይወቱ አስጊ የሆነ ጉዳት ደርሶበት በሆስፒታል ሕክምና ሲደርግለት ቆይቶ በኋላ ላይ ሕይወቱ ማለፉን የአሜሪካው የቢቢሲ አጋር ሲቢኤስ ኒውስ አረጋግጧል። የኒው ዮርክ ፖሊስም አዛሬሎ መሞቱ በሆስፒታሉ ባልደረቦች ቅዳሜ ጠዋት እንደተገለጸለት ኤንቢሲ ዘግቧል።




አዛሬሎ ራሱ ላይ እንዲህ ዓይነት ጭካኔ ለምን እንደፈፀመ ግልጽ አይደለም። መርማሪዎች ክስተቱን አስመልክቶ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ በ911 የአደጋ ጊዜ የጥሪ ማዕከል ተደውሎላቸው አንድ ግለሰብ ራሱን ሊያቃጥል እንደሆነ እንደተነገራቸው ገልጸዋል።

አዛሬሎ ይኖርበት ከነበረው ፍሎሪዳ ወደ ኒው ዮርክ ያመራውም ባለፈው ሳምንት ነበር። ግለሰቡ ከዚህ በፊት በኒው ዮርክ የሠራው ወንጀል እንደሌለ እና በፍሎሪዳ የሚኖሩ ቤተሰቦቹ ወደ ኒው ዮርክ ማቅናቱን እንደማያውቁም ተገልጿል።

የኒውዮርክ ፖሊስ አዛዥ ጀፍሪ ማድሬይ እንዳሉት አዛሬሎ ተቀጣጣይ ፈሳሽ እና በራሪ ወረቀቶችን ይዞ ወደ ሥፍራው ከማቅናቱ በፊት በአካባቢው በሚገኝ መናፈሻ ውስጥ ሲዘዋወር ነበር።

የበተናቸው በራሪ ወረቀቶች ፕሮፖጋንዳ ላይ የተመሠረቱ እንደሆኑ የገለጹት የፖሊስ አዛዡ፣ 'የሴራ ይዘት' ያላቸው ናቸው ብለዋል። በትራምፕ ችሎት ምክንያት በፍርድ ቤቱ አካባቢ በርካታ የፀጥታ አካላት የነበሩ ሲሆን የፖሊስ መኮንኖች እሳቱን ለማጥፋት ወደ መናፈሻው በፍጥነት ነበር ያመሩት።

በእሳት ክፉኛ የተቃጠለውን አዛሬሎን በማንሳት ወደ አካባቢው ወደሚገኝ የቃጠሎ ሕክምና ማዕከል መወሰዱን ፖሊስ ገልጿል። ሦስት የኒውዮርክ ፖሊስ መኮንኖች እና አንድ የፍርድ ቤት ባለሥልጣን እሳቱን ለማጥፋት ሲሞክሩ ቀላል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

ጁሊ በርማን የተባሉ የዓይን ምስክር " . . . ምንም ትርጉም የሚሰጥ አይደለም፤ ሁሉም ነገር በፍጥነት የሆነ ነበር። ምን እየተካሄደ እንዳለ ለማወቅ 20 ሰከንድ ፈጅቶብኛል" ሲሉ ለጋዜጠኞች ተናግረዋል።

ከአደጋው በኋላ መርማሪዎች በሥፍራው ተገኝተው ግለሰቡ ራሱን ከማቃጠሉ በፊት የበተናቸውን ወረቀቶች ሲሰበስቡ ታይተዋል። መርማሪዎቹ የዓይን እማኞችን እያነጋገሩ ሲሆን ግለሰቡ ራሱን ከማቃጠሉ በፊት የተናገረው ነገር እንደሌለ ገልጸዋል።

በአሜሪካ ግለሰቦች ራሳቸውን ሲያቃጥሉ ይህ የመጀመሪያው አይደለም። የካቲት ወር ላይ ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ከሚገኘው የእስራኤል ኤምባሲ ፊት ለፊት አንድ የአሜሪካ የአየር ኃይል አባል ራሱን በእሳት ያቃጠለ ሲሆን በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## ኬንያ ኢታማዦር ሹሟን የገደለውን የሄሊኮፕተር አደጋ መንስኤ ለማወቅ መርማሪ ቡድን አሰማራች

የኬንያ መንግሥት የሀገሪቷን ኢታማዦር ሹም ጄኔራል ፍራንሲስ ኦጎላ እና ሌሎች ዘጠኝ መኮንኖችን የገደለውን የሄሊኮፕተር አደጋ መንስኤ ለማወቅ ወደ ሥፍራው መርማሪ ቡድን ላከ። እስካሁን የአደጋው ምክንያት ግልጽ አይደለም።

ሐሙስ ዕለት ከሰዓት በኋላ ለመብረር ከተነሳ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ወዲያውኑ በተከሰከሰው ሄሊኮፕተር ውስጥ ተሳፍረው ከነበሩ 12 መኮንኖች መካከል ጄኔራል ኦጎላ አንዱ ነበሩ። በአደጋው ሕይወታቸው ያለፉ ሰዎች አስከሬን ወደ ናይሮቢ የተላከ ሲሆን ከአደጋው የተረፉት ሁለት መኮንኖችም በሆስፒታል ሕክምና እየተደረገላቸው ይገኛል።

ባለ አራት ኮከብ ማዕረጉ ጄኔራል የቀብር ሥነ ሥርዓትም ዛሬ እሑድ በትውልድ ቀያቸው በምዕራብ ሲያ ካውንቲ እንደሚፈፀም ቤተሰቦቻቸው አሳውቀዋል። አደጋውን ተከትሎ የሦስት ቀን ብሔራዊ የኀዘን ቀን ያወጁት ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ " ህልፈታቸው ለአገሪቷ ትልቅ ኀዘንን የፈጠረ ነው" ብለዋል።

ፕሬዚዳንቱ ዋና የጦር አማካሪያቸው በግዳጅ ላይ እያሉ ሕይወታቸው ማለፉን ገልጸዋል።" እናት ሀገራችን ጀግና የሆኑ ጄኔራሎቿን፣ የጦር መኮንኖቿን፣ ወታደሮቿን አጥታለች" ሲሉ ለኔሽን ጋዜጣ ተናግረዋል። የተቃዋሚ ፓርቲ መሪው ራይላ



**ጄኔራል ፍራንሲስ ኦጎላ**

ኦዲንጋም አደጋውን " የኬንያ አሳዛኝ ቀን" ሲሉ ገልጸውታል።

የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ሊቀ መንበር ሙሳ ፋኪ ማሃማት አሳዛኙን የሄሊኮፕተር አደጋ ተከትሎ ለኬንያ ፕሬዚዳንት፣ መንግሥት እና ሕዝብ" ኀዘናቸውን ገልጸዋል። ጄኔራል ኦጎላ የኬንያ መከላከያ ኃይል ኢታማዦር ሹም ሆነው የተሾሙት ባለፈው ዓመት ሚያዚያ ወር ላይ ነበር።

በኬንያ መከላከያ ሚኒስቴር ድረ ገጽ ላይ እንደሰፈረው መረጃ ከሆነ ጄኔራል ኦጎላ እንደ አውሮፓውያኑ ሚያዝያ 24 ቀን 1984 ነበር የመከላከያ ኃይልን የተቀላቀሉት። በዚህም በሚቀጥለው ሳምንት በጦሩ ውስጥ ያሳለፉትን 40ኛ ዓመት ይደፍኑ እንደነበር ቢቢሲ ዘግቧል።


## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ፡-የፌ/ጠ/ፍ/ቤት እና በተከሳሽ፡- ፈትሂ ኢዘዲን ባሻ መካከል ባለው የወንጀል ክስ ክርክር ጉዳይ ኮንትሮባንድ ተከሳሽ በ16/08/2016 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት 9ኛ ገቢዎች እና ጉምሩክ ወንጀል ችሎት እንዲቀርቡ ካልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንደሚቀጥል ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ/ፍ/ባለመብት ፅሜክስ ግሎባል ኢንተርፕራይዝ እና በተከሳሾች/በፍ/ባለእዳዎች እነ አቶ ቀለሙ ዕቁባይ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክስ ጉዳይ በተከሳሽ/ በፍ/ባለእዳ 2ኛ መድሃኔ ብርሃኑ አብርሃ በ16/8/2016 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ ምድብ 4ኛ ልዩ ልዩ ችሎት እንዲቀርቡ እንገልፃለን፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤት ቁጥር 221 ግብር ከፋይ (TIN) 0085517130 የሚታወቀው ዳዊት ቢኒያም እና ጓደኞቻቸው ፓርኪንግ አገልግሎት ህ/ሽ/ማህበር በሚል በግብር ክስ ከፋይነት ከተመዘገብንበት ከልደታ ክ/ከ/አ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ከምንጠቀምባቸው ደረሰኞች ውስጥ ከቁጥር ከ0001-0250 ያልተሠራበት የእጅ በእጅ የመክፈያ ደረሰኝ ስለጠፋብኝ በማናቸውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሠራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል። ይሁን ከደረሰኙ ውስጥ ተሠርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈጸመ በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩባት ለልደታ ክ/ከአ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርጉ እናስታውቃለን፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ዳዊት ሰለሞን**

## የሒሳብ ምርመራ ጨረታ ማስታወቂያ

ፍቅር 1ኛ ደረጃ ከፍተኛ አገር አቋራጭ አውቶብስ የግል ባለንብረቶች ማህበር የ2013፣ የ2014፣ የ2015 እና የ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት ሂሳብ በውጪ ኦዲተሮች ማስመርመር ይፈልጋል፡፡

**በመሆኑም ተጫራቾች፡-**

1) የንግድ ፈቃድ ያላቸው፤

2) በሙያው ብቃትና ሕጋዊነት ታውቆ በመንግስት የተመዘገቡ፤

3) የዘመኑን ግብር የከፈሉ፤

4) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር(TIN)ያላቸው፤

5) ሕጋዊ የሒሳብ ምርመራ ፈቃድ ያላቸው፤

6) በትራንስፖርት ድርጅቶች የሒሳብ ምርመራ ያከናወነ፤

ማስረጃውን ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ5 ተከታታይ የሥራ ቀናት አዲስ ከተማ ክፍለ ክ/ከተማ በሚገኘው ከፍተኛ አገር አቋራጭ አውቶቡሶች መናኸሪያ ቢሮ ቁጥር 8 መረጃችሁን ማቅረብና መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር፡- 09 11 60 55 26 መጠየቅ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

**ፍቅር 1ኛ ደረጃ ከፍተኛ አገር አቋራጭ አውቶብስ የግል ባለንብረቶች ማህበር**

# ስፖርት




# ትዕግስት አሰፋ በለንደን ማራቶን ክብረወሰን ለማሻሻል ተዘጋጅታለች

**አስማረዩሁ ግዛው**

በየዓመቱ በአለም ከሚካሄዱ ታላላቅ ማራቶን ውድድሮች አንዱ የሆነው የለንደን ማራቶን ዛሬ ሲካሄድ ኢትዮጵያዊት አትሌት ትዕግስት አሰፋ የውድድሩን ክብረወሰን ለመስበር ትሮጣለች፡፡ ውድድሩ ለ44 ጊዜ ሲካሄድ የርቀቱ የዓለም ክብረወሰን ባለቤቷ ትዕግስት አሰፋ፣ አልማዝ አያና፣ ትዕግስት ከተማ፣ መገርቱ ዓለሙ እና የዓለም ዘርፍ የኋላው ከኬንያዊያን አትሌቶች ጋር የሚያደርጉት ፉክክር ይጠበቃል፡፡

በወንዶቹ አንጋፋው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ፣ ሞስነት ገረመው፣ ታምራት ቶላ፣ ዳዊት ወልዴ፣ ልዑል ገብረስላሴ፣ ሴይፉ ቱራ እና ሚልኬሳ መንገሻን የመሳሰሉ ታላላቅ አትሌቶች የሚያደርጉት ፉክክርም በጉጉት ይጠበቃል፡፡

በዛሬው ውድድር በእንግሊዛዊቷ አትሌት ፓውላ ራድክሊፍ 2፡15፡25 ተይዞ የቆየውን የውድድሩን ክብረወሰን ለመስበር ከሚሮጡት አትሌቶች መካከል ትዕግስት አሰፋ እና ኬንያዊት ብሪጊድ ኮስጌ ብርቱ ፉክክር እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፡፡ ውድድሩን የማሸነፍ ቅድመ ግምት የተሰጣት ትዕግስት አሰፋ ባለፈው መስከረም ወር በተካሄደው የበርሊን ማራቶን በአስደናቂ ሁኔታ የዓለም ክብረወሰን በመጨበጥ ስታጠናቅቅ፤ ቀደም ሲል ኬንያዊቷ ብሪጊድ ኮስጌይ ያስመዘገበችውን ክብረወሰን በመስበር ነበር፡፡

እልህ አስጨራሽ ፍልሚያ በሚጠበቅበት የዛሬው የለንደን ማራቶን የርቀቱን የዓለም ክብረወሰን የጨበጠችው ትዕግስት ከተሳካላት ውድድሩን 2 ሰዓት ከ10 ደቂቃ በመጨረስ የራሷን ዓለም ክብረወሰን ለመስበር ዝግጅት ማድረጓን ተናግራለች፡፡ አትሌቷ በርሊን ላይ ክብረወሰኑን የጨበጠችው 2 ሰዓት ከ11 ደቂቃ ከ53 ማይክሮ ሰከንድ በመሮጥ ነበር፡፡ በጀርመን ዋና ከተማ ይህን ስትሮጥ በብሪጊድ ኮስጊ ያስመዘገበችውን የአለም ክብረወሰንን በሚያስደንቅ ሁኔታ በመስበርም ጭምር ነው።

ትዕግስት ለውድድሩ ያደረገችው ዝግጅት እና ክብረወሰኑን ለመስበር ያላትን ዕቅድ አስመልክታ ሃሳቧን እንዲህ በማለት ገልጻለች፡፡ “ወደ ፊት ከሁለት ሰአት ከአስር ደቂቃ በታች መሮጥ እፈልጋለሁ”። “ያንን ለማድረግ የሚያስችለኝን ልምምድ ማድረግ ከቻልኩ ዋናው ነገር ያ ይሆናል። እግዚአብሔር ቢፈቅድ በዛ መንገድ መሄድ እችላለሁ ብዬ አስባለሁ። ለንደን ውስጥ ውድድር ለማድረግ በጣም ጓጉቻለሁ። ባለፈው አመት ማራቶንን እዚህ ለመሮጥ አስቤ ነበር፣ ነገር ግን ተጎድቻለሁ። ይህ ደግሞ በዚህ ጊዜ የበለጠ እንድወስን አድርጎኛል” በማለት ተናግራለች፡፡

ባጋጠማት የጅማት ጉዳት ምክንያት “ከትራክ ሯጭነት ወደ ማራቶን መቀየሩ ቀላል አልነበረም” ትላለች። ብዙ ጠንክሮ መሥራት ይፈልግ ነበር እናም ወዲያውኑ አልሰራም ግን አሁን በጣም ቀላል እና የበለጠ ተፈጥሯዊ ስሜት ይሰማኛል፡፡” ስትልም ተናግራለች፡፡

ትዕግስትና እና ኮስጌ በለንደን የሚፋለሙት ከ2019 የአለም ቻምፒዮና ሩት ቼፕንጌቲች፣ የኦሊምፒክ ቻምፒዮን ፔሬስ ጄፕቺርቺር እና የ2022 የለንደን ማራቶን አሸናፊዋ ያለምዘርፍ የኋላው ጋር ሲሆን፤ ይህም በታሪክ ከአራቱ ፈጣን ሴቶች መካከል ሦስቱ በውድድሩ ውስጥ ይገኛሉ ማለት ነው። ውድድሩ በአትሌቶች ምርጫ ስኬታማ በመሆኑ የዓለም ክብረወሰን ይመዘገብበታል ተብሎም ይጠበቃል፡፡ በውድድሩ ክብረወሰን እንዲሰበር አሯሯጮች ትልቅ የቤት ስራም ይጠብቃቸዋል፡፡



አትሌት ትዕግስት አሰፋ የለንደን ማራቶንን ክብረወሰን ለመስበር መዘጋጀቷን ገልጻለች፤

የለንደን ማራቶን ዳይሬክተር ሂዩ ብራሸር ከውድድሩ መጀመር አስቀድመው በሰጡት አስተያየት “በሴቶች የማራቶን ሩጫ ወርቃማ ዘመን ላይ ነን። በበርሊን ባለፈው አመት ባሳየችው አስደናቂ ሩጫ የአለም ክብረወሰንን በላቀ ደረጃ ያሳደገችው ትዕግስት አሰፋን ጨምሮ ሌሎች አራት ሴቶች ይሳተፋሉ። ሆኖም ትዕግስት፣ ኮስጌ እና እንደ ሩት ቼፕጌቲች፣ ፔሬስ ጄፕቺርቺር እና ያለምዘርፍ የኋላው በአጠቃላይ አስር ሴቶች ከ2 ሰአት ከ17 ደቂቃ ከ30 ሰከንድ በታች የሮጡበት እንደሚሆን አልጠራጠርም” በማለት ገልጸዋል።

በወንዶች ውድድር በታሪክ ሶስተኛው ፈጣኑ የማራቶን ሰዓት ባለቤት፣ የኦሊምፒክ፣ የዓለም ቻምፒዮና እና የሀገር አቋራጭ ንጉስ ቀነኒሳ በቀለ አሸንፎ በፓሪስ ኦሊምፒክ ለመጨረሻ ጊዜ ሀገሩን የሚወክልበት እድል ለመፍጠር ይሮጣል፡፡ አንጋፋው አትሌት ፊቱን ከመም ወደ ጎዳና ውድድሮች ካዞረ በኋላ በርካታ ጊዜ ድል ማድረግ ችሏል፡፡ ቀነኒሳ ከወራት በፊት አትሌት ሲሳይ ለማ ፈጣን ሰዓት አስመዝግቦ ባሸነፈበት የቫሌንሲያ ማራቶን ተሳትፎ በማድረግ በአንጋፋ አትሌቶች ተይዞ የነበረውን ክብረወሰን በእጁ አስገብቷል፡፡

“በማራቶን አሁንም የተሻለ መስራት እንደሚችል አእምሮዬ ይነግረኛል፣ በጣም ብዙ ግቦች አሉኝ። ኦሊምፒክ ከፊታችን ነው፡፡ ምናልባት ፓሪስ የመጨረሻ ኦሊምፒክ ሊሆን ይችላል” በማለት ለአሸናፊነቱ ያለውን ተስፋ ገልጿል።

የቀድሞ የርቀቱ የዓለም ቻምፒዮንና የኒውዮርክ ማራቶን አሸናፊ ታምራት ቶላ፣ በታሪክ ሰባተኛ ፈጣን ሰዓት ባለቤት የሆነው ሞስነት ገረመውና ዳዊት ወልዴን ጨምሮ ስድስት ጥሩ ሰዓት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ወንድ አትሌቶች ይሮጣሉ፡፡


## SECOND ROUND INVITATION TO BID

**Procurement Reference Number: OIT/Bid-05/2016 E.C**

ODAA Integrated Transport S.C has allocated funds, to be used for the procurement of Consultancy Services and invites all eligible local Consultants for:

* Name of Project:-Consultancy Service Of Design Adaption & Modification of ODAA INTEGRATED TRANSPORT S.C FOR AMBO ODAA FUEL SERVICE STATION.
*. Location (Zone);-Ambo Town
* Estimated Area: 4,385m2
*. Bid Bond Amount (ETB):-50,000.00 ETB
* Only Consultants Registered in Ethiopia, as Consulting Architects & Engineers Category Five & above is Eligible.
* The bid Security should be in the form of Unconditional Bank Guarantee or CPO

Generally, the bid security shall be valid for 120 days after bid opening date and...

1. Interested Bidders shall submit the following evidence and other appropriate documents demonstrating the bidder's compliance:
* Renewed Certificate of Competency from Concerned Authority,
*Trade license and Consultancy Professional License valid and renewed for 2016 Ethiopian Calendar year,
*VAT & Tax Registration Certificate issued by the tax authority,
*Tax Clearance certificate issued from the Tax Authority (Inland Revenue Authority) which allows the bidder to participate in public tenders at the date of the deadline for bid submission.
*Registered in Supplier's List Public Procurement and Property Administration Agency (FPPPAA)
2.The bidders shall obtain a complete set of bidding documents by paying non-refundable fee of ETB 1,000.00 (One thousand Birr) from OIT S.C's Head Office at the address given below during Working Hours(From Monday to Friday at 2:00-6:00PM &7:00-11:00AM local time) from the first date bids announced by newspaper (Addis Zemen) within Forteen(14) consecutive days.
3. Bidding will be conducted through the National Competitive Bidding (NCB) procedures and is open to all eligible domestic bidders as specified and defined in the bidding document.
4. The Technical Proposal shall be marked as “ORIGINAL” and “COPY”. The original and copy of the Technical Proposal shall be placed in a sealed envelope clearly marked “TECHINICAL PROPOSAL”.
5. Bid Security shall be presented sealed in a separate envelope clearly marked as “BID SECURITY”
6. The Financial Proposal shall be marked “ORIGINAL” and “COPY” as appropriate. The original and copy of the Financial Proposal shall be placed in a sealed envelope clearly marked “FINANCIAL PROPOSAL” followed by the procurement reference number and the bidding documents prepared in English Language
7. Bid closing date shall be on 15th day as of this announcement at 4:00PM local time and opened on the same date at 4:30 PM local time.
8. Finally, the whole documents shall be placed in a single wax-sealed envelope whose outer cover contains all necessary information about the firm & Employer including project information, and submitted on or before 15th Days at 4:00PM local time.
9. Bids must be delivered to the address below on the date and time mentioned above. Late bidders will be rejected. Technical Proposals will be opened by the Procurement and Supply Directorate of the Bureau in the presence of bidders' representatives who choose to attend, at the address below on the same date at 4:30PM local time,. If the bide Opening date(15th day)is holiday or on Sunday the Opening date will be Next working day.
10. The Financial Proposal of qualified bidders will be opened, at the same address given below, on the date that is to be declared by OIT s.c, after the completion of the evaluation of Technical Proposals.
11. The Company reserves all right to accept or reject any bids at any time prior to contract award without incurring any liability to Bidders.

* Further Information could be Obtained from the following:

**Address:Addis Abeba,Sub city: Nifas Silk Lafto,woreda:02,Mekannisa S.Sara Tower 5th Floor, around Amigo Caffe,**
**Phone No.251-922-248-258**

**ODAA Integrated Transport S.C**




# የጎበዞቹ ተማሪዎች ምክር

**እየሩስ ተስፋዬ**

እንዴት ናችሁ ልጆችዬ? ሳምንቱን ትምህርታችሁን በሚገባ በመከታተል እንዳሳለፋችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም። ልጆችዬ ዛሬ የእረፍት ቀናችሁ ነው አይደል? የዛሬዋን ቀን በማንበብ፣ በጥናትና በጨዋታ እንደምታሳልፉ ተስፋ አደርጋለሁ። ለዛሬ ምን ልናቀረብንላችሁ የፈለግን ይመስላችኋል? በትምህርታቸው ጎበዝ የሆኑ ልጆችን በማነጋገር ለእናንተ ያስተላለፉትን ቆንጆ ምክር ነው እሺ ልጆች።

ተማሪ በአምላክ አለማየሁ ትባላለች:: በመጀመሪያው መንፈቅ አመት በትምህርቷ ሁለተኛ ነው የወጣችው:: ወደፊት ሳይንቲስትና መምህር መሆን ትፈልጋለች:: ሳይቲስት ሆና ሀገሯን የማገልገል ህልምም አላት። የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን ባላት የትርፍ ጊዜ መሞከር ያስደስታታል።

መምህር መሆን የፈለገችበት ምክንያት ደግሞ ፍትህንና ሌሎች መሰል ጉዳዮችን ለማስማር እንደሚቻል በማሰብ ነው። ታዲያ ልጆችዬ ተማሪ ባምላክ ይህን ፍላጎቷን ለማሳካት በርትታ ትምህርቷን እየተከታተለች ትገኛለች።

ሰብሪን ነቢል ደግሞ የአራተኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ወደፊት ትምህርቷን ጨርሳ ዶክተር መሆን ትፈልጋለች:: የሚወልዱ እናቶችን የማገልገል ሃሳብም አላት:: ልጆችዬ ሃሳቧ እንዲሳካለት ሰበሪን ዘወትር ታነባለች፣ ታጠናለች፣ ያልገባትንም መምህሮቿን ትጠይቃለች:: ሰብሪን ለሌሎች ተማሪዎች የምታስተላልፈው መልዕክት አላት:: መልዕክቷ ምን መሰላችሁ? ትምህርታችሁን በደንብ ተከታተሉ፣ ወላጆቻችሁ የሚሏችሁን ነገር ስሟቸው፣ ታዘዟቸው፣ አክብሯቸው የሚል ነው:: ልጆችዬ ጥሩ መልዕክት ነው አይደል? በሚገባ እንደምትሉ ተስፋ አደርጋለሁ።


ተማሪ ልያት ሙስቀን


ተማሪ ሄኖክ ቀጸላ

በመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት በትምህርቷ አንደኛ የወጣችውን ተማሪ እናስተዋውቃችሁ:: ስሟ አርሴማ ወርቅነህ ይባላል:: የሦስተኛ ክፍል ተማሪ ናት:: በርትታ በማጥናቷና በትኩረት በማንበቧ በትምህርቷ አንደኛ መውጣት ችላለች:: አርሴማ ተጠቀመችበት የራሷ የሆነ የአጠናን ስልት ውጤታማ አድርጓታል:: ሌሎች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በትኩረት ትምህርታቸውን ቢከታተሉ፣ቢያጠኑና በትኩረት ቢያነቡ እንደእሷ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ ትናገራለች:: ጨዋታ መቀነስ እንዳለባቸውም ትመክራለች:: ወላጆችም ልጆቻቸውን መደገፍ እንዳለባቸው ትናገራለች:: ለወደፊት ሳይንቲስት የመሆን ፍላጎት ያላት አርሴማ ተመራማሪ ሆና ሀገሯን የማስጠራት ፍላጎት አላት::

ሌላኛዋን ተማሪ ደግሞ እናስተዋውቃችሁ። ተማሪ ልያት ሙለቀን አራተኛ ክፍል ናት:: እድሜዋ አስር ነው:: ከዚህ ቀደም በትምህርቷ ስምንተኛ ነበር የወጣችው:: አሁን ደግሞ ስድተኛ ወጥታለች:: ልያት ደረጃዋን ያሻሻለችው በርትታ በማጥናቷ እና በትኩረት በማንበቧ እንዲሁም የእናቷን ምክር በመስማቷ፣ከጎበዝ ልጆች ጋር በጋራ በመረዳዳቷ ነው:: ከዚህ የበለጠ በማጥናት ዶክተር የመሆን ፍላጎትም አላት::

ተማሪ ልያት ለልጆች የምለው አለኝ ትላለች:: ልጆች እንደ ጌም እና ቴሌቪዥን ያሉ ነገሮች ትኩረታቸውን እንደሚስብ ባውቅም እንደማይጠቅማቸው በመገንዘብ ትምህርታቸው ላይ ብቻ ማተኮር አለባቸው ትላለች:: እርሷ በሳይንስና ቴክሎጂ ክበብ በተጨማሪ በግብረ ገብ ክበብ በንቃት ትሳተፋለች:: በነዚህ ክበባት በመሳተፏ ብዙ ጥቅም አግኝታበታለች:: በሳይንስና ቴክኖሎጂው ስለሳይንስ ብዙ እንድታውቅ ረድቷታል:: በግብረ ገብ ክበብ በማሳተፏ ደግሞ ሥነ ሥርዓት መልካም ስነ ምግባር ተምሬበታለሁ ትላለች::

ሌላኛው ጎበዝ ተማሪ ሄኖክ ቀጻላ ይባላል። የአንደኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን፤ በትምህርቱ አንደኛ የወጣ ጎበዝ ተማሪ ነው። ልጆችዬ እናንተ ልምድ እንድትቀስሙ በማሰብ እንዴት አንደኛ ወጣህ ብለን ጠይቅነው። ምላሹም ምን መሰላችሁ? ክፍል ውስጥ በሚገባ ትምህርቱን በመከታተሉ፣ከትምህርት ቤት ሲመለስም በማጥናቱና ፈተና ሲደርስ ደግሞ በሚገባ በመዘጋጀቱ እንደሆነ ይናገራል። ለወደፊት ሳይንቲስት የመሆን ፍላጎት ያለው ሲሆን የሕዋ ምርምሮችን በማድረግ ችግሮችን ለመፍታት ያልማል። ሌሎች ተማሪዎችም እንደርሱ ጎበዝ እንዲሆኑ በርትተው እንዲያጠኑና ጨዋታ እንዳያበዙ ይመክራል። የእርሱ ወላጆች እንደሚደግፉት የሚናገረው ጎበዙ ተማሪ ሄኖክ ወላጆች ልጆቻቸውን መደገፍ እንዳለባቸው ይመክራል።

ልጆችዬ የጎበዝ ተማሪዎችን መልዕክት እንዴት አገኛችሁት? ምንስ ተማራችሁ? "በርትተን ማጥናት እንዳለብን፣በክፍል ውስጥ በንቃት መከታተል እንዳለብን፣ጨዋታ አለማብዛት፣ያልገባንን መጠየቅ እንዳለብን፣የወላጆቻችንን እና የመምህሮቻችን እገዛ ማግኘት እንዳለብን በሚገባ ተምረናል" የሚል ምላሽ እንደምትሰጡ እናምናለን:: ልጆችዬ መልካም የእረፍት ቀን እንዲሆንላችሁ እንመኛለን:: ሳምንት እስከምንገናኝ ሰላም!!